# የፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠና ማዕከል

**ለረጅም ጊዜ የስራ ላይ ሰልጣኞች የተዘጋጀ**
**የስልጠና ማኑዋል**

# የወንጀል ቅጣት አወሳሰን

**በፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠና ማእከል የተዘጋጀ**

# ማውጫ

መግቢያ ........ 3
ክፍል አንድ ........ 4
የቅጣት አላማ፣ ግብና የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች ........ 4
1. የቅጣት አላማና ግብ ........ 4
2. የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች ........ 5
3. በኢትዮጵያ የቅጣት አወሳሰን ህጉና ልምዱ፣ ........ 5
3.1. ቅጣትን የሚመለከቱ የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ይዘት ........ 5
3.2. የቅጣት ውሳኔዎች ግምገማ ........ 7
4. የሌሎች አገሮች ልምዶች ........ 8
ክፍል ሁለት ........ 14
የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ........ 14
1. የመመሪያው አላማና ግብ ........ 14
2. የቅጣት እርከን ሰንጠረዥ ........ 14
2.1. ነጻነትን የሚያሳጡ ቅጣት እርከን ሰንጠረዥ ........ 14
2.2. የገንዘብ መቀጮን የሚመለከተው ሰንጠረዥ፣ ........ 16
3. መመሪያው የሚመራባቸው አጠቃላይ ድንጋጌዎች፣ ........ 16
4. በመመሪያው መሰረት ቅጣት የሚወሰንበት ሁኔታ፣ ........ 18
4.1. የወንጀል ደረጃዎችን እንደወንጀሉ ከባድነት መለየት፣ ........ 19
4.2. የመነሻ ቅጣት አወሳሰን፣ ........ 21
4.3. ደረጃ ለወጣላቸው ወንጀሎች ቅጣት አወሳሰን ዝርዝር አሰራር ማሳያ ........ 25
4.4. ደረጃ ላልወጣላቸው ወንጀሎች የቅጣት አወሳሰን ........ 37
4.5. የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ በሚኖርበት ጊዜ የቅጣት አሰላል፣ ........ 39
4.6. የቅጣት አሰላል ቅደም ተከተል (በማሳያ ምሳሌዎች ተደግፍ የቀረበ፣) ........ 42
4.7. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ........ 47
4.8. የንብረት ግምት በተመለከተ ........ 47
ማጠቃለያ ........ 48
ዋቢ ሰነዶች (በኢንተርኔት የሚገኙ) ........ 49

# መግቢያ

በወንጀል ሕግ አንቀጽ 88 ንኡስ አንቀጽ 4 የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ እንዲያወጣ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የተወሰኑ የወንጀል ጉዳዮች ማለትም ከ80 በመቶ ያላነሱ የወንጀል መዝገቦችን የሚይዙ የወንጀል ድንጋጌዎች ተመርጠው ጥናት ሲደረግ ቆይቶ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ከግንቦት 9 ቀን 2002 ጀምሮ ተግባራዊ የሚሆን መመሪያ አውጥቷል፡፡

መመሪያውን ለማዘጋጀት የተለያዩ አገሮችን ልምዶች ለማግኘት ሙከራ ተደርጓል፡፡ ከተሞክሮዎች ልምድ በመውሰድ  የተዘጋጁት የቅጣት መወሰኛ መመሪያዎች በወርክሾፕም ዳብረዋል፡፡ ቀጥሎም ለፍትህ ስርአት ማሻሻያ ቦርድ ቀርቦና ውይይት ተደርጎባቸው ተቀባይነት አግኝተዋል፡፡ በተደጋጋሚ አውደጥናቶችና ስልጠናዎች  የተገኙ ግብአቶችን አካቶ የመጨረሻው መመሪያ ወጥቷል፡፡

ይህ ጽሁፍ የተዘጋጀው ስለመመሪያው ግንዛቤ ለመፍጠር እና በመመሪያው መሰረት ቅጣት እንዴት እንደሚወሰን የጋራ መግባባትን ለመፍጠር ነው፡፡ ጽሁፉ ሁለት ክፍል ያለው ሲሆን በክፍል አንድ በአጠቃላይ ስለቅጣት አወሳሰን የወንጀል ህጉን ድንጋጌዎች፣ የቅጣት አወሳሰን ልምድና ተሞክሮ እንዲሁም በሌሎች አገሮች የቅጣት አወሳሰን በአጭሩ ለማሳየት የሚሞክር ሲሆን፣ በክፍል ሁለት የቅጣት አወሳሰን መመሪያው የሚመራባቸው መሰረታዊ መርሆዎች፣ ለቅጣት አወሳሰን መመሪያው የተመሰረተባቸው እምነቶች (assumptions) እና በመመሪያው መሰረት ቅጣት እንዴት እንደሚሰላ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

ይህ ጽሁፍ ለውይይት መነሻ የሚሆን ሀሳብ የሚያቀርብ ሲሆን፣ በስልጠና በሚገኘው ግብአት በቀጣይነት ሊሻሻልና ሊዳብር የሚችል ነው፡፡

## ከስልጠናው የሚጠበቁ ውጤቶች

## ይህንን ስልጠና ሲያጠናቅቁ ሰልጣኞች፣

1. ቅጣት አወሳሰንን በተመለከተ በወንጀል ህጋችን ስላሉት ድንጋጌዎች ያላቸውን እውቀትና ግንዛቤ ያዳብራሉ፡፡
2. ቅጣት አወሳሰንን በተመለከተ በአገራችን ያለው ልምድ ምን እንደሆነና በወንጀል ህጉ ከተመለከተው ድንጋጌና ስርአት ጋር ያለውን ግንኙነት መርምረው ይረዳሉ፡፡
3. በቅጣት አወሳሰን የተለያዩ አገራት ልምዶችን በተመለከተ መጠነኛ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡
4. የቅጣት አወሳሰን መመሪያው የሚመራባቸው መሰረታዊ መርሆዎችና ድንጋጌዎችን ተረድተው ማስረዳት ይችላሉ፡፡
5. በመመሪያው መሰረት ቅጣት ለመወሰን የሚያስችል ክህሎት ያዳብራሉ፡፡

# ክፍል አንድ

# የቅጣት አላማ፣ ግብና የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች

## 1. የቅጣት አላማና ግብ

በወንጀል ህግ አንቀጽ 1 የወንጀል ህግ አላማና ግብ ተደንግጓል፡፡

### የወንጀል ህግ አንቀጽ 1

የወንጀል ሕጉ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፣ የህዝቦቹን፣ የነዋሪዎችን፣ ሰላም፣ ደህንነት፣ ስርዓት፣ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው፡፡

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡ ፣ ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ፣ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፅሙ እርምጃዎችን በመውሰድ ነው፡፡

ይላል፡፡

ከድንጋጌው ሁለተኛ ፓራግራፍ መረዳት የሚቻለው የቅጣት አላማ ወንጀልን መከላከል እንደሆነ፣ ስለሆነም የወንጀል ህግ ግብን ማሳካት እንደሆነ፣

የቅጣቱም ግብ፣

- ወንጀል አድራጊው ሌላ ወንጀል እንዳይፈጽም የሚያደርግ (prevention)
- ሌሎችን ወንጀል ከመፈጸም እንዲቆጠቡ የሚያደርግ (deterrence)
- ወንጀል አድራጊን ማረም (rehabilitaiton )

እንደሆነ እንረዳለን፡፡

## 2. የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች

ቅጣት ሲወሰን በመሰረቱ ተመሳሳይና ተቀራራቢ ወንጀሎች በተመሳሳይ መልኩ ቅጣት ሊያርፍባቸው ይገባል፡፡ እንደወንጀሉ ክብደት ደግሞ ቅጣቱም ተመጣጣኝ መሆን አለበት፡፡ ስለሆነም ቅጣት የተፈለገውን ውጤት ያመጣ ዘንድ የሚመራባቸው መርሆዎች አሉት፡፡ እነርሱም፣

- ወጥነት (uniformity)
- ተመጣጣኝነት (proportionality)
- ግልጽነትና ተጠያቂነት (transparency and accountability)
- ተገማችነት (predictability)

ናቸው፡፡

## 3. በኢትዮጵያ የቅጣት አወሳሰን ህጉና ልምዱ፣

### 3.1. ቅጣትን የሚመለከቱ የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ይዘት

በህጉ ሁለተኛ ታላቅ ክፍል (ልዩ ክፍል)፡፡ ለእያንዳንዱ የወንጀል ድርጊት መነሻና መድረሻ ቅጣት ተቀምጠዋል፡፡

አብዛኛዎቹ የቅጣት መነሻና መድረሻዎች የሚከተሉትን ይመስላሉ፡፡

- ከ1 አመት እስከ 10 አመት
- ከ3 አመት እስከ 10 አመት
- ከ5 አመት እስከ 15 አመት

በሀጉ ልዩ ክፍል ከተመለከቱት ቅጣቶች በተጨማሪ አጠቃላይ የቅጣት አወሳሰን ድንጋጌዎች አሉ፡፡

- አንቀጽ 88 (የቅጣቶች አወሳሰን)
- አንቀጽ 84 (ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃዎች)
- አንቀጽ 82 (ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያዎች)
- አንቀጽ 85 (ልዩ የቅጣት ማክበጃዎች)
- አንቀጽ 83 (ልዩ የቅጣት ማቅለያዎች)
- ከአንቀጽ 179-189 (ቅጣቱ ሲከብደና ሲቀል ስለሚጣለው ቅጣት መጠን)
- ከአንቀጽ 190-200 (ቅጣትን ስለመገደብ) ናቸው፡፡

እነዚህን የተለያዩ ድንጋጌዎች መሰረት አድርጎ ቅጣት እንዴት ይወሰናል?

በወንጀል ህግ አንቀጽ 189(1) የሚከተለው ተደንግጎ እናገኛለን፡፡

‹በአንድ ወንጀል ላይ ቅጣት የሚያከብዱና የሚያቃልሉ ጠቅላላ ምክንያቶች በተደራረቡ ጊዜ ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ ማክበጃ ምክንያቶቹን ከግምት በማስገባት ያከብድና ቀጥሎ የሚያቃልሉትን ምክንያቶች መሰረት አድርጎ ቅጣቱን ያቃልላል›

ይላል፡፡

ከዚህ መረዳት እንደምንችለው መጀመሪያ ለማክበድ ከየት ይነሳል? የሚል ጥያቄ እንድናነሳ ያደርገናል፡፡ ስለሆነም በግልጽ ባይቀመጥም ዳኛው፣

- በቅድሚያ መነሻ ማስቀመጥ እንደሚኖርበት፣
- ቀጥሎ ማክበጃ ምክንያቶች ከአሉ ቅጣቱን ማክበድ እንደሚኖርበት፣
- ቀጥሎ ማቅለያ ምክንያቶች ከአሉ ቅጣቱን ማቅለል እንደሚኖርበት፣

ያስረዳል፡፡

ይሁንና፣

- መነሻው ስንት ይሁን? በሕጉ መልስ የለም፡፡
- ማክበጃዎች ሲኖሩ በምን ያህል ሊከብድ ይገባል ? በሕጉ መልስ የለም፡፡
- ማቅለያዎች ሲኖሩ በምን ያህል ሊቀል ይገባል ? በሕጉ መልስ የለም፡፡

ስለሆነም በወንጀል ህጉ የተቀመጡትን የቅጣት ድንጋጌዎችና ስለቅጣት አወሳሰን የተቀመጡት ድንጋጌዎች በፍርድ ቤት የሚሰጡ ቅጣቶች፣

- ወጥነት፣
- ትክክለኛነት ያለው፣

ለማድረግ የሚያስችሉ አይደሉም፡፡

## 3.2. የቅጣት ውሳኔዎች ግምገማ

ቅጣት የተሰጠባቸው መዝገቦችን ስንመለከት፣

አቃቤ ህግ፣

- ቅጣቱ ከብዶ ይወሰን፣
- ተመጣጣኝ ቅጣት ይሰጠው፣

ከሚል ባለፈ ከብዶ ሲባል ከባዱ ምን ያህል እንደሆነ፣

- መነሻው ስንት ሆኖ ሊከብድ እንደሚገባ፣
- ተመጣጣኝ የሚሆነው ምን እንደሆነ ፣

የሚያመለክቱ አይደሉም፡፡

በተከሳሽ በኩል የሚቀርቡ የቅጣት አስተያየቶችም ጥቅል ሆነው ከሚቀርቡ በስተቀር ተመሳሳይ ችግር ያለባቸው ናቸው፡፡

ዳኛው ቅጣትን ሲወስንም፣

ቅጣትን ለማክበድ፣

- የወንጀል ሪከርድ አለው
- የወንጀል አፈጻጸሙ አደገኛነት አለው፣
- ድርጊቱ የተፈጸመው በአፍቅሮ ንዋይ በመሆኑ የሚሉ ምክንያቶችን በመጥቀስ፣

ቅጣቱን ለማቅለል

- የወንጀል ሪከርድ የለውም ስለሆነም አደገኛ አይደለም፡፡
- የቤተሰብ አስተዳዳሪ ነው፡፡ ወዘተ የሚሉ ምክንያቶችን በመጥቀስ፣

ቅጣት ይወስናል፡፡

ይሁንና ዳኞች እነዚህን ምክንያቶች ይጥቀሱ እንጂ፣

- በየትኛውም መዝገብ ቅጣቱን ለመወሰን መነሻው ስንት መሆን እንዳለበት ተመልክቶ አይታይም፡፡
- በማክበጃነት የቀረቡትንና በማቅለያነት የቀረቡትን ምክንያቶች የሚቀበለውና የሚቀበሉትንና የማይቀበሉትን ከለዩ በኋላ፣ ከምክንያቶቹ ጋር ግንኙነቱን ለማስረዳት በማይቻል መልኩ በጥቅሉ የቅጣቱ መጠን ይቀመጣል፡፡

ስለሆነም፣

- መነሻ የቅጣት መጠኑ ስንት እንደሆነ፣
- በማክበጃነት የተቀመጡት ምክንያቶች ቅጣቱን በማክበድ ያላቸው አስተዋጽኦ እንዲሁም
- ማቅለያ ምክንያቶች እንዴት አገልግለው ቅጣቱ እንደቀለለ፣

ለማወቅ አይቻልም፡፡

ከዚህ አጠቃላይ ግንዛቤ በመነሳት በአገራችን ቅጣት አወሳሰን ምክንያታዊነት የጎደለው፣ በእርግጥም የተጣለው ቅጣት አግባብነት ያለው መሆኑን ለማስረዳት አይቻልም፡፡ በዚህም ምክንያት፣

1. በአንድ ዳኛ በተለያየ ጊዜ ወይም በተለያዩ ዳኞች ተቀራራቢና ተመሳሳይ ለሆኑ ወንጀሎች የሚሰጡ የተለያዩ ቅጣቶች መኖራቸው፣
2. ከዚህም የተነሳ በቅጣት አወሳሰን ተገማችነት የሌለው መሆኑ፣
3. ቅጣት አወሳሰን ግልጽነት የሌለውና በፍትህ አካላቱ ባለሙያዎች ላይ ተጠያቂ ለማድረግ የማያስችል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

## 4. የሌሎች አገሮች ልምዶች

የአገራችን የወንጀል ህግ ስርአትና አቀራረጽ በኮንቲኔንታል የህግ ስርአት እንዳለው የሕግ አቀራረጽ በኮድ የተዘጋጀ ነው፡፡ ይሁንና በኔዘርላንድ ካለው የተወሰነ ተሞክሮ በስተቀር በሌሎቹ ተመሳሳይ የህግ ስርአት ባላቸው አገራት ቅጣት አወሳሰን በመሰረቱ አሁን በአገራችን ካለው የተለየ አይደለም፡፡

የኮመንሎው የህግ ስርአት ተከታይ በሆኑ አገሮች በተነጻጻሪ ዝርዝር የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አዘጋጅቶ ተግባራዊ የማድረግ ተሞክሮና ልምድ አለ፡፡ በአሜሪካ በፌዴራል እንዲሁም በክልል (ስቴትስ) የዳበረ የቅጣት አወሳሰን ጋይድላይን ዝግጅትና በዚሁ መሰረት የመስራት የዳበረ

ልምድ አለ። በእንግሊዝ በተመሳሳይ መልኩ በየወንጀል አይነቱ የቅጣት ጋይድላይን አዘጋጅቶ ቅጣት የሚወሰንበት የዳበረ ልምድ አለ።

ለማሳያ ያህል የአሜሪካን ፌዴራሉን ጋይድላይን እና የኔዘርላንድን እንመልከት፣

__አሜሪካ__

በአሜሪካ ከ1970ዎቹ በፊት የቅጣት አወሳሰን ስርአቱ indeterminate sentencing ተብሎ ይታወቅ የነበረ ነው።

የወንጀል ጥፋት የፈጸመ ሰው እና የጤና ችግር ያለበት ሰው በተመሳሳይ መልኩ መታየት አለባቸው የሚል አመለካከት ገዢ አስተሳሰብ የነበረበት ጊዜ ነበር። ስለሆነም ሀኪም በሽተኛውን አክሞ ለማዳን ለጤናው ችግር ምክንያቱ ምንድነው ብሎ አጥንቶ ህክምና በመስጠት እንደሚያድነው ሁሉ በወንጀል ጥፋተኛ የሆነ ሰውም እንደበሽተኛ በመታየት በተመሳሳይ ታክሞ መዳን አለበት የሚለው አስተሳሰብና ፍልስፍና (ማስተማርና ማረም) የበላይነት ያገኘበት ጊዜ ነበር።[1]

ዳኛው ቅጣት ሲወስን ጥፋተኛው የሚቀጣበትን ሬንጅ ያስቀምጣል (ለምሳሌ ከ10-20 አመት) ወይም ጣሪያውን ብቻ ያስቀምጣል (እስከ 20 አመት)። ፖሮል ኮሚሽን የሚባል ተቋም ጥፋተኛው በዳኛው ከተወሰነበት ከፍተኛው የቅጣት ጣሪያ (1/3ኛ) ከጨረሰ በኃላ የፍርደኛውን ሁኔታ እየገመገመ በዚሁ እንዲያበቃ ወይም ከጣሪያው ሳይበልጥ ቅጣቱን እንዲጨምር ሊወስን ይችላል። በዚህ መልኩ ከሞላ ጎደል በነበረው ልምድ አጥፊው ከተጣለበት ቅጣት ጣሪያ 15 በመቶ ብቻ ነበር በማረሚያ ቤት የሚቆየው።[2]

በ1960ዎቹ አካባቢ ወንጀል ከመቀነስ እና በቁጥጥር ስር ከመዋል ይልቅ እየጨመረ መምጣቱ፣ ለዳኞች እና ፓሮል ኮሚሽን ስልጣንን አላግባብ የመገልገልና በታራሚዎች ላይ አድልዎ

[1] sentencing guideline, judicial discretion, and crimes (internet material) page 3 ተመልከት
[2] ከላይ የተጠቀሰው፣ ገጽ 5

እየተፈጸመ ነው የሚለው አመለካከት እየተስፋፋ መምጣቱና ሌሎች ምክንያቶች ተደራርበው ይህ አይነቱ የቅጣት አወሳሰን ስርአት ጥያቄ ውስጥ እየገባ እንዲመጣ አድርጓል፡፡[3]

ይህ ወንጀል አድራጊዎች በተገቢው ሁኔታ ቅጣት ማግኘት አለባቸው የሚለው እንቅስቃሴ ምክንያት ሆኖ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ተጀመረ፡፡ የፌዴራሉ መንግስት ቅድሚያውን ቢወስድም ስቴትስ (ወይም የክልል መንግስታት) ይህንን በመከተል የየራሳቸውን የቅጣት መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ ጀምረዋል፡፡

የፌዴራል መንግስቱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ (sentencing guideline) በጣም ዝርዝር የሆነ (583 ገጽ ያለው) ነው፡፡ በጋይድላይኑ መሰረት ፍርደኞች ቢያንስ 85 በመቶ ያላነሰውን በዳኛ የተወሰነውን ፍርድ መጨረስ አለባቸው፡፡

ጋይድላይኑ ቅጣትን ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው በመነሻውና በመድረሻው መካከል ከ6 ወር ያላነሰ፣ ከ25 በመቶ ያልበለጠ ሬንጅ ባለው 43 እርከኖች የተከፋፈለ ደረጃዎች (offence level) አለው፡፡ ከወንጀል አድራጊው ያለፈ የህይወት ታሪኩ ጋር በተያያዘ ወደጎን በአምስት እርከኖች የተከፋፈለ ነው፡፡[4]

<u>የቅጣት አወሳሰን በመመሪያው መሰረት፣</u>

1. በቅድሚያ ከተፈጸመው ወንጀል አንጻር በመመሪያው በተመለከተው መስፈርት መሰረት የትኛው የወንጀል ደረጃ (offence level) ላይ እንደሚወድቅ ይለያል፡፡
2. ሌሎች ቅጣቱን የሚያከብዱ እና የሚያቀሉ ምክንያቶች እየታዩ እርከኑ ከፍ ወይም ዝቅ ይላል፡፡

ለምሳሌ ሌብነትን ብንወስድ፣

- በሌብነት የተገኘው ጥቅም እስከ ብር 5000 ከሆነ የወንጀል ደረጃው offence level እርከን 6 ነው፡፡ (ከ0-6 ወራት)
- ከ5000-10000 ከሆነ በሁለት እርከን ጨምሮ መነሻው እርከን 8 ይሆናል፡፡(ከ0-6 ወራት)

[3] ከላይ የተጠቀሰው፣ ገጽ 6
[4] አባሪውን ይመልከቱ፣

- ከ10000-30000 ከሆነ በአራት እርከን ጨምሮ መነሻው እርከን 10 ይሆናል፡፡(ከ6-12 ወራት)
- ከ2.5 ሚሊዮን በላይ ከሆነ 18 እርከን ጨምሮ መነሻው ሌቭል 24 ይሆናል፡፡ (ከ51-63 ወራት)(4 አመት ከ3 ወር-5 አመት ከ3 ወር)

በህይወት ታሪኩ መሰረት ደረጃው ወደጎን ይለያል፡፡

ለምሳሌ፣

- ከአንድ አመት ያላነሰ የታሰረ ከሆነ ለእያንዳንዱ ቅጣት 3 ነጥብ ይኖረዋል፡፡
- ከ60 ቀናት ያላነሰ የታሰረባቸው ለእያንዳንዱ ቅጣት 2 ነጥብ ይኖረዋል፡፡ ወዘተ፣

እነዚህን በመደመር የሚገኝ ነጥብ ይኖራል፡፡

ውጤቱ (0-1) ወይም (2-3)፣(4-6) ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ መሰረት ወደጎን ያለው እርከን ይታወቃል፡፡

ሁለቱ የሚገናኙበት ሳጥን (የቅጣት ሬንጅ) ቅጣት የሚጣልበት ሬንጅ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ዳኛው በዚህ ሬንጅ ውስጥ ቅጣቱን ይጥላል፡፡

በአሜሪካ በተለያዩ ስቴትስ የተለያዩ የቅጣት አወሳሰን መመሪያዎች አሉ፡፡ በሁሉም የአሜሪካ ስቴትስ መመሪያውን ከማክበር አንጻር በዳኞች ላይ የተጣለው ግዴታ ተመሳሳይ አይደለም፡፡ ዳኞች መመሪያውን ተከትለው ከመስራት አንጻር የመከተል ግዴታቸውን በተመለከተ ወይም ጥብቅነቱን በተመለከተ በአራት ከፍሎ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ እነርሱም፣

- በመመሪያው ከተቀመጠው ሬንጅ መውጣት በፍጹም የተከለከለበት፣
- በመመሪያው ከተቀመጠው ሬንጅ መውጣት ይቻላል፣ ይሁንና ዳኛው ምክንያቱን ማስቀመጥ እንደሚኖርበትና ይህም በይግባኝ ታይቶ ሊሻር የሚችልበት፣
- በመመሪያው ከተቀመጠው ሬንጅ መውጣት ይቻላል፣ ይሁንና ዳኛው ምክንያቱን ማስቀመጥ እንደሚኖርበት፣
- ምክንያት መስጠት ሳያስፈልግ ከጋይድላይኑ ውጭ መወሰን የሚቻልበት[5]

---

5

**ኔዘርላንድ፣**

በኔዘርላንድ ለማንኛውም ወንጀል ዝቅተኛው መነሻ አንድ ቀን ነው፡፡ በዝርዝር ህግ ሌላ ጣሪያ ካልተቀመጠ ጣሪያው 15 አመት ነው፡፡ የወንጀል ህጉ ለማንኛውም ወንጀል በመቀጮ መቅጣትን ያደፋፍራል፡፡ በእስር ለሚደረግ ቅጣት ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ዳኛው ምክንያት እንዲያስቀምጥ ያዛል፡፡ ዳኛ እስርን ሲወስን ብቻ ሳይሆን የእስር ጊዜውን መጠን ለምን እንደወሰነ ምክንያት እንዲያስቀምጥ ህጉ ያዛል፡፡[6]

በኔዘርላንድ የቅጣት አወሳሰን ወጥነት የሌለውና ተገማች አለመሆኑ አሁንም ችግር ነው፡፡ ይሁንና በተወሰኑ የወንጀል አይነቶች በቅጣቶች መካከል ልዩነቶች ዝቅተኛ እንደሆኑ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ ለዚህም በጠቅላይ አቃቤ ህጎች ቦርድ የወጣ አቃቤ ህጎች የቅጣት የውሳኔ ሀሳብ ሲያቀርቡ የሚመሩበት መመሪያ እንደሆነ ይጠቀሳል፡፡ በመመሪያው ለእያንዳንዱ የወንጀል ድርጊት ምን ያህል ነጥብ ሊሰጠው እንደሚገባ የተቀመጠ ሲሆን፣ አቃቤ ህጎች የቅጣት አስተያየት ሲያቀርቡ ይህንን መመሪያ ተከትለው ነው፡፡

ለምሳሌ

- ለብስክሌት ስርቆት 10 ነጥብ፣
- መኖሪያ ቤት ገብቶ መስረቅ 60 ነጥብ፣
- የተጠቀመበት መሳሪያ 5 ነጥብ ያስጨምራል፡፡
- በወንጀል ሰለባው ላይ ጉዳት ማድረስ ሌላ 10 ነጥብ ያስጨምራል፡፡
- ሙከራ ከሆነ ደግሞ ነጥቡ ይቀንሳል፡፡
- ደጋጋሚነት ነጥቡን በግማሽ ያሳድጋል፡፡ ወዘተ

እነዚህን በማዳመርና በመቀነስ ነጥቡ ከ1 ጀምሮ-ይኖራል፡፡

ከእነዚህ ውስጥ

- እስከ 180 ነጥብ ያለው እንዳለ ይወሰዳል፡፡
- ከ181-540 ያሉት እያንዳንዱ ነጥብ የአንድ ነጥብ ግማሽ(1/2ተኛ) ይወሰዳሉ፡፡
- ከ541 በላይ ያሉት እያንዳንዱ ነጥብ የአንድ ነጥብ ሩብ (1/4ተኛ ) ይወሰዳሉ፡፡

በዚህ መሰረት የተገኘው ነጥብ ተደምሮ የትኛው ነጥብ ላይ እንደሚያርፍ ይታወቃል፡፡ እያንዳንዱ ነጥብ (22 ዩሮ መቀጮ ወይም 1 ቀን እስራት ወይም የ2 ሰአት ግዴታ ስራ ያስከትላል)

[6] sentencing guidelines around the world, (internet material), p 36-38

ስለሆነም አቃቤ ህጉ በአጠቃላይ፣

- የተገኘው ነጥብ ከ30 ነጥብ በታች ከሆነ ከመክሰስ ይልቅ መቀጮ እንዲከፍል ወይም የግዴታ ስራ እንዲሰራ ያደርጋል፡፡
- ከ30-60 ከሆነ የግዴታ ስራ እንዲሰራ እንዲታዘዝ ሊከስ ይችላል፡፡
- ከ60 በላይ ሲሆን በየነጥቡ ደረጃ የተቀመጠ የቅጣት መጠን ለምሳሌ ከ120 ነጥብ በላይ ከሆነ እስራት እንዲቀጣ ከነመጠኑ የቅጣት ውሳኔ አስተያየት ያቀርባል፡፡

ፍርድ ቤት የአቃቤ ህጉን ሀሳብ የመቀበል ግዴታ የለበትም፡፡ ይሁንና መመሪያ በወጣላቸው የወንጀል አይነቶች ፍርድ ቤቶች የአቃቤ ህጉን የቅጣት አስተያየት ተከትለው የሚወስኑ መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

በአንዳንድ የቅጣት አወሳሰን መመሪያዎች አቃቤ ህጉ የቅጣት ሀሳቡን ሲያቀርብ ከተቀመጠው መመሪያ ውጭ ከሆነ ምክንያት እንዲያቀርብ ይጠየቃል፡፡ በአንዳንዶቹ ምክንያት ማስቀመጥ ግዴታ አልተጣለበትም፡፡ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት አቃቤ ህግ ምክንያት የማቅረብ ግዴታ በሌለበት የወንጀል አይነቶች ላይ ከአቃቤ ህግ አቃቤ ህግ ልዩነቱ የሰፋ ነው፡፡

አቃቤ ህግ በመመሪያው ከተቀመጠው ወጥቶ የቅጣት አስተያየት የሚያቀርብባቸው እየተሰባሰቡ መመሪያውን ለማሻሻል ይውላሉ፡፡ አቃቤ ህጉ በመመሪያው ከተቀመጠው በጣም በተራራቀ መልኩ የቅጣት አስተያየት አቅርቦ ከሆነ ከአቃቤ ህጉ ጋር ውይይት ይደረግበታል፡፡ ተጠያቂነትም ያስከትላል፡፡[7]

[7] ከላይ የተጠቀሰው፣

## ክፍል ሁለት

## የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002

### 1. የመመሪያው አላማና ግብ

በመመሪያው አንቀጽ 3 የሚከተለው ተደንግጎ እናገኛለን፡፡

**አንቀጽ 3 . የመመሪያው አላማና ግብ፣**

1. የመመሪያው አላማ በወንጀል ፍትህ ስርአቱ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ባረጋገጠ መልኩ ውጤታማና ተገማችነት ያለው ቅጣት የሚሰጥበትን ስርአት በመመስረት ወንጀል እንዳይፈጸም መከላከል ነው፡፡
2. መመሪያው የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፡፡
   ሀ. በተቀራራቢና ተመሳሳይ የወንጀል ጉዳዮች መካከል ተቀራራቢነት ያለው የቅጣት አወሳሰን (ወጥነትን) ማረጋገጥ፣
   ለ. እንደወንጀሉ ክብደትና አደገኛነት መሰረት ተመጣጣኝ ቅጣት ያለው የቅጣት አወሳሰን ማረጋገጥ ነው፡፡

### 2. የቅጣት እርከን ሰንጠረዥ

በመመሪያው ቅጣትን ለመወሰን ዝርዝር ሰንጠረዦች ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህም ነጻነትን የሚያሳጡ ቅጣት ሰንጠረዥ እና የገንዘብ መቀጮ ሰንጠረዥ በሚል ተከፋፍለዋል፡፡

### ሀ. ነጻነትን የሚያሳጡ ቅጣት እርከን ሰንጠረዥ

ይህ በመመሪያው አባሪ አንድ ሆኖ ተያይዞ የሚገኝ ሰንጠረዥ ሲሆን የወንጀል ሕጉን ዝቅተኛ የቅጣት መነሻ (1 ቀን የግዴታ ስራ) እና ከፍተኛውን የሞት ቅጣት መሰረት በማድረግ 39 ደረጃዎች ያሉት የቅጣት እርከኖች እንዲኖሩት ሆኖ የተዘጋጀ ነው፡፡

የቅጣት ሰንጠረዡ አላማና ግብ በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ለእያንዳንዱ ወንጀል የተቀመጠው መነሻ እና ጣሪያ ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ ፍቅድ ስልጣን (range or discretion)

ውስጥ የተለያዩ የቅጣት እርከኖችን በማዘጋጀት በተመሳሳይና ተቀራራቢ የወንጀል ጥፋቶች ተቀራራቢ ቅጣት ለመጣል የሚያስችል ሁኔታ በመፍጠር በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88(4) የታሰበውን ውጤት ማምጣት ነው፡፡ ስለሆነም የወንጀል ሕጉ ባስቀመጠው አጠቃላይ ማእቀፍ ውስጥ ዝርዝር አሰራሩን ለመደንገግ የወጣ የወንጀል ህጉ ያስቀመጣቸውን የቅጣት መርሆዎችና ድንጋጌዎች ማስፈጸሚያ ተደርጎ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡

ሰንጠረዡ ሲዘጋጅ ለእያንዳንዱ የቅጣት እርከን መነሻና መድረሻ ያለው ሲሆን፣ የሚከተሉትን መሰረተ ሀሳቦች መሰረት ባደረገ መልኩ የተዘጋጀ ነው፡፡

1. የቅጣት መነሻቸው ከዝቅተኛው ጀምሮ ከፍ እያለ ሲሄድ በመነሻውና በመድረሻው መካከል በተነጻጻሪ እያደገ የሚሄድ ፍቅድ ስልጣን (range) እንዲኖረው ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡ (ሬንጁ ዝቅተኛው 3 ወር ሲሆን ከፍተኛው 5 አመት ነው፡፡
    - የቅጣት እርከን(level) 1 ሬንጁ 3 ወር(በትክክል 2 ወር ከሃያ ቀን) ሆኖ ደረጃ በደረጃ እያደገ ይሄዳል፡፡
    - ከቅጣት እርከን 12 ማለትም (ከ2 አመት- 2 አመት ከ6 ወር) ጀምሮ ሬንጁ ከስድስት ወር ያላነሰ ነው፡፡
    - ከቅጣት እርከን 21 ማለትም (ከ5 አመት መነሻ) ጀምሮ ሬንጁ ከአንድ አመት ያላነሰ ነው፡፡
    - ከቅጣት እርከን 29 ማለትም (ከ10 አመት መነሻ) ጀምሮ ሬንጁ ከሁለት አመት ያላነሰ ነው፡፡
    - ከቅጣት እርከን 34 ማለትም (ከ15 አመት መነሻ) ጀምሮ ሬንጁ ከሶስት አመት ያላነሰ ነው፡፡

2. በየደረጃው ያለው የቅጣት እርከን መነሻ ሲቀመጥ፣ ከቅጣት እርከኑ ዝቅ ብሎ ከነበረው የቅጣት እርከን አማካይን መነሻ በማድረግ የቅጣት መነሻና መድረሻው ተወስኗል፡፡
3. ለዚህ መመሪያ አላማ የአንድ ቀን እስራት ከአንድ ቀን (8 ሰአት) የግዴታ ስራ ጋር ተመጣጣኝ ተደርጎ ተወስዷል፡፡[8] ስለሆነም በመመሪያው አባሪ አንድ ከእርከን 1-3 ድረስ ለማሳያነት እስራትና የግዴታ ስራ በአማራጭ ተለይተው ተቀምጠዋል፡፡

[8] በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 103 እስከ ስድስት ወር የቀላል እስራት ቅጣት እስከ ስድስት ወር ሊደርስ በሚችል የግዴታ ስራ ሊቀየር እንደሚችል ስለሚያመለክት የአንድ ቀን ቀላል እስራትና የአንድ ቀን ግዴታ ስራ እኩል

4. በቅጣት ማቅለያ ጊዜ የእስራት ቅጣት ወደመቀጮ እንደሚቀየር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 179 የሚደነግግ በመሆኑ ወደመቀጮ ሲቀየር ስንት ሊሆን እንደሚችል በሚያሳይ መልኩም የቅጣት እርከኑ ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህ መሰረት በመመሪያው አባሪ አንድ ሰስተኛ አምድ (column) የመቀጮ መጠን ተመልክቷል፡፡[9]

## ለ. የገንዘብ መቀጮን የሚመለከተው ሰንጠረዥ፣

የገንዘብ መቀጮን በሚመለከት የተዘጋጀው ሰንጠረዥ አላማና ግብ ነጻነትን የሚያሳጡ የእስራት ቅጣቶችን ለመወሰን ከተዘጋጀው ሰንጠረዥ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ሰንጠረዡ ሲዘጋጅ የሚከተሉትን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

1. ሰንጠረዡ ሲዘጋጅ መነሻ ያደረገው በአንቀጽ 90(1 ) የተመለከተውን ከፍተኛ ጣሪያ እስከ ብር 500000 ያለውን በመውሰድ ነው፡፡ በዚህ መሰረት የገንዘብ መቀጮ ከዝቅተኛው ጣሪያ 1000 ብር እስከ ብር 500 ሺህ ሊደርስ በሚችል መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡[10]

2. ዝቅተኛ መነሻ ግን ለሁሉም እርከኖች ተመሳሳይ በህጉ የተመለከተው ነው (10 ብር እና 100 ብር)፡፡ የዚህም ምክንያቱ መቀጮን ለመወሰን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 90(2) የተዘረዘሩት የተለያዩ ምክንያቶች መሰረት እንደየወንጀል አድራጊው ገቢ መጠን እንዲወሰን ስለሚደነግግ፣ በዚህ ምክንያትም እንደሁብቱና ገቢው ሁኔታ መቀጮ የማይጣልበት ሁኔታ ሊኖርም እንደሚችል ታሳቢ በማድረግ ለሁሉም ዝቅተኛው በህጉ የተመለከተው ተመሳሳይ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

## 3. መመሪያው የሚመራባቸው አጠቃላይ ድንጋጌዎች፣

1. በወንጀል ሕግ 189 (1) ፍርድ ቤቶች ቅጣትን ሲወስኑ መጀመሪያ ማክበድ እንደሚገባቸው ቀጥለው ደግሞ ማቅለያ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ ማቅለል

---

ተደርጎ ተወስዷል፡፡ የስራ ሰአቱን በሚመለከትም በአገራችን ያለው መደበኛ የቀን የስራ ሰአት ከ8 ሰአት ያልበለጠ ስለሆነ ከዚህ ባልበለጠ መልኩ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡

[9] የመቀጫውን መጠን ለመወሰን ታሳቢ የተደረገው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 90(3) ተቀጪው የሕግ ሰውነት ያለው በሆነ ጊዜ እስራቱ ወደመቀጮ እንደሚቀየር እና ለዚህ ሲባል የአምስት አመት ቀላል እስራት ወደ ብር 10000 መቀጮ ይቀየራል የሚለውን መሰረት በማድረግ የእስራት ጊዜው ሲቀንስ መቀጮውም ስለሚቀንስ በዚህ ግምት መሰረት የመቀጮው መጠን እየተስተካከለ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡

[10] በቅጣት መመሪያው አባሪ ሁለትን ተመልከት

እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ይህም ዳኞች ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን መሰረት አድርገው ቅጣት ከመወሰናቸው በፊት መነሻ ቅጣት ማስቀመጥ እንደሚገባቸው ያመለክታል፡፡ ስለሆነም በመመሪያው መሰረት ቅጣት ሲወሰን በቅድሚያ መነሻ ቅጣትን በመወሰን ይጀምራል፡፡ የመመሪያው ዝርዝር ድንጋጌዎችም ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ የተዘጋጁ ናቸው፡፡

2. በወንጀል ህጉ አንቀጽ 88 ንኡስ አንቀጽ 4 ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቅጣት አወሳሰን ወጥነትና ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ መመሪያ እንደሚወጣ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በመነሳትም ወንጀሎችን በተመሳሳይ ደረጃ የሚያስቀምጣቸውን ባህርይ መሰረት በማድረግ ለተመሳሳይ ወንጀሎች ተመሳሳይና ተቀራራቢ ቅጣት መቅጣት (ወጥነትን)፣ እንዲሁም የወንጀል ፍሬነገሩ ተመሳሳይ ቢሆንም እንደወንጀሉ ከባድነትና አደገኛነት ደረጃዎችን በማውጣት ቅጣት መቅጣት ( ተመጣጣኝነትን/ትክክለኛነትን) ለማረጋገጥ እንዲቻል በተመሳሳይ የወንጀል ድንጋጌ ውስጥ ቢወድቁም ለወንጀሎች እንደክብደታቸው የወንጀል ደረጃ ሊወጣላቸውና በዚህ መሰረት ቅጣቱ ሊወሰን እንደሚገባ ያስቀምጣል፡፡ ይህንን መሰረት በማድረግም መነሻ ቅጣቱን ለመወሰን በቅድሚያ የወንጀል ደረጃውን መለየት እንደሚገባ መመሪያው ያስቀምጣል፣ ዝርዝር ድንጋጌዎቹም ይህንን ለመወሰን በሚያስችል መልኩ የተደነገጉ ናቸው፡፡

3. ህግ አውጪው ለእያንዳንዱ የወንጀል ድርጊት የቅጣት መነሻና መድረሻ ያስቀመጠ ሲሆን፣ ይህም እንደወንጀሉ ሁኔታ ከመነሻው ጀምሮ ቅጣቱ ሊወሰን እንደሚችል የሚያሳይ ነው፡፡ ስለሆነም በወንጀሉ ከባድነት ወይም አፈጻጸም በተነጻጻሪ ቀላል የሚባለው በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል የተደነገገው መነሻ ጀምሮ የመነሻ ቅጣቱ ሊወሰን እንደሚችልና እንዲሁም እንደወንጀሉ ከባድነት ደረጃ በደረጃ እያደገ በሚሄድ መልኩ ቅጣቱ ሊወሰን እንደሚገባው ያስቀምጣል፡፡ ስለሆነም ዝርዝር ድንገጌዎቹ ለተለያዩ የወንጀል ደረጃዎች የተለያየ መነሻ እንዲኖራቸው በሚያደርግ መልኩ የተዘጋጁ ናቸው፡፡

4. ህግ አውጪው በወንጀል ልዩ ክፍሉ ለእያንዳንዳንዱ ወንጀል ያስቀመጠው ጣሪያ ላይ የሚደረሰው ጠቅላላ ማክበጃ ምክንያቶች ሲኖሩ እንደሆነ አንቀጽ 183 ያመለክታል፡፡[11] ስለሆነም ማክበጃ ምክንያቶችን መሰረት አድርጎ ቅጣቱ ከመክበዱ በፊት የሚቀመጠው መነሻ ቅጣት የወንጀሉ ከባድነት ከፍ ያለ ቢሆንም (በህጉ ካልተወሰነ በስተቀር (ለምሳሌ

[11] ቅጣቱ እንዲከብድ ህጉ በደነገገ ጊዜ (84) ለቅጣቱ ማክበጃ የሆኑትን ምክንያቶች አይነትና ብዛት እንዲሁም ወንጀለኛው የፈጸመውን ጥፋት ከባድነት በማመዛዘን ፍርድ ቤቱ በዚህ ሕግ ልዩ ክፍል በተመለከተው አግባብነት ባለው ድንጋጌ ከተወሰነው ቅጣት ጣሪያ ሳያልፍ ቅጣቱን ይወስናል፡፡ (አንቀጽ 183)

ያህል በሞት ይቀጣል፣ በእድሜ ልክ እስራት ይቀጣል በሚል መልኩ ካልተቀመጠ[12]) ጣሪያው ላይ አይደርስም። የመመሪያው ዝርዝር ድንጋጌዎች በተነጻጻሪ ከሁሉም ከፍተኛና ከባድ ለተባለው የወንጀል ደረጃ መነሻ ቅጣቱ ሲቀመጥ በልዩ ክፍሉ ከተመለከተው ጣሪያ ዝቅ ብሎ እንዲወሰን በሚያስችል መልኩ የተቀመጡ ናቸው።

5. በተመሳሳይ የቅጣት እርከን ላይ ለሚገኙ ወንጀሎች በቅጣት ማክበጃና ማቅለያ መሰረት የሚኖረው ጭማሪ ወይም ቅነሳ ተመሳሳይ ሊሆን ይገባል። የመመሪያው ዝርዝር ድንጋጌዎች ይህንን መርሆ ተግባራዊ ማድረግ በሚችል መልኩ የተዘጋጁት።
6. መመሪያው ለወንጀሎች የሚቀመጠውን ቅጣት መጠን አያስቀምጥም። ነገር ግን ዳኞች መነሻ ቅጣቱንም ሆነ ቅጣቱ ሲከብድ ወይም ሲቀል ቅጣቱን ሊወስኑበት የሚችሉትን ፍቅድ ስልጣን (range) ያስቀምጣል። ስለሆነም ዳኞች በተቀመጠው ፍቅድ ስልጣን (range) ከመነሻው እስከ መድረሻው በመመሪያው ያልተመለከቱ የወንጀል ድርጊቱን ልዩ ባህርያት መሰረት አድርገው ቅጣትን መወሰን ይችላሉ ማለት ነው።
7. መመሪያው በወንጀል ህጉ የተቀመጡትን የቅጣት አወሳሰን ድንጋጌዎች ለማስፈጸም የሚወጣ በመሆኑ፣ በወንጀል ህጉ ውስጥ የተቀመጡትን አጠቃላይ መርሆዎችና ድንጋጌዎች መሰረት አድርጎ እየተተረጎመ ሊሰራበት እንደሚገባ ያስቀምጣል። ስለሆነም በወንጀል ሕጉ በቅጣት አወሳሰን ጊዜ የተቀመጡ በርካታ ድንጋጌዎች ከዚህ ጋር እየተናበቡ ይሰራባቸዋል ማለት ነው። ለምሳሌ በማክበጃ ምክንያትነት የተቀመጡት ወንጀሉን ማቋቋሚያ በሆኑ ጊዜ በድጋሚ ቅጣትን ለማክበድ እንደማይውሉ ይደነግጋል። ቅጣትን ስለመገደብ የተመለከቱ ድንጋጌዎች በወንጀል ህጉ ውስጥ አሉ። ስለሆነም መመሪያው እነዚህንና ሌሎች በወንጀል ህጉ የተደነገጉ ድንጋጌዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ ሊሰራበት ይገባል ማለት ነው።

## 4. በመመሪያው መሰረት ቅጣት የሚወሰንበት ሁኔታ፣

በሰንጠረዡ መሰረት ቅጣትን ለመወሰን በመጀመሪያ የሚነሳው መሰረታዊ ጥያቄ በዚህ ሰንጠረዥ መሰረት ቅጣትን እንዴት እንወስናለን የሚለው ነው። ማለትም፣

1. መነሻ ቅጣት እንዴት እንወስናለን?
2. በማክበጃዎች መሰረት እንዴት እንወስናለን ?

[12] ለምሳሌ አንቀጽ 671(2)

3. በማቅለያዎች መሰረት እንዴት እንወስናለን ?

የሚሉት ናቸው፡፡

ከዚህ በላይ ስለአጠቃላይ መመሪያው ስለተመሰረተባቸው ድንጋጌዎች በተመለከተው ጽሁፍ ውስጥ እንዳየነው መነሻ ቅጣቱን ለመወሰን በቅድሚያ የወንጀል ደረጃውን መለየት እንደሚገባ ያስቀምጣል፡፡ ስለሆነም በመጀመሪያ ሊመለስ የሚገባው ጥያቄ የወንጀል ደረጃው እንዴት ይወሰናል? የሚለው ነው፡፡

## 4.1. የወንጀል ደረጃዎች የተወሰነበት መነሻ ሀሳብ፣

በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88(2) ዳኛው ቅጣትን ሲወስን የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን፣ ያለፈ የህይወት ታሪኩን፣ ወንጀሉን ለማድረግ ያነሳሱትን ምክንያቶችና የሀሳቡን አላማ፣ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈጻጸሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን ነው ይላል፡፡

በዚህ ድንጋጌ የተመለከቱት ምክንያቶች የሚያመለክቱት የተፈጸመው ወንጀልና የተጣሰው የወንጀል ድንጋጌ አንድ ቢሆንም በዚህ ድንጋጌ ውስጥ ከተመለከቱት ምክንያቶች መሟላትና አለመሟላት አንጻር ቅጣት በተለያዩ ወንጀል አድራጊዎች መካከል ሊለያይ እንደሚችል ነው፡፡ ተመሳሳይ አይነት ወንጀል ሆኖ አንዱ ወንጀለኛ ዝቅተኛ ቅጣት ሲቀጣ ሌላው ደግሞ ከባድ ቅጣት ሊቀጣ እንደሚችል የሚያመለክት ነው፡፡ ይህም ወንጀሉ ተመሳሳይ ቢሆንም የተለያየ የከባድነት ደረጃዎች ሊኖሩት እንደሚችሉ የሚያመለክት ነው፡፡ ለዚህም ነው በወንጀል ሕጉ በቅጣት መነሻውና ጣሪያው መካከል ከፍተኛ ልዩነት እንዲኖር የተደረገው፡፡ (ለምሳሌ ከ1 አመት እስከ 10 አመት፣ ከ1 አመት እስከ 15 አመት ወዘተ..)

ከዚህ በመነሳትም መመሪያው የተፈጸመው ወንጀል አንድ የወንጀል ህጉን ድንጋጌ የሚጥስ ቢሆንም ወንጀሉ እንደክብደቱ ደረጃዎች ሊወጡለት የሚችሉ መሆኑን ታሳቢ ባደረገ መልኩ የወንጀል ደረጃዎች ለተለያዩ የወንጀል አይነቶች አዘጋጅቷል፡፡

በመመሪያው መሰረት ለወንጀሎች የተለያየ የወንጀል ደረጃ ሲወጣ ግን በአንቀጽ 88(2) ያሉትን ምክንያቶች በሙሉ በመስፈርትነት አልተጠቀመም፡፡ ምክንያቱም በድንጋጌው የተቀመጡት እነዚህ ምክንያቶች በተለያዩ የወንጀል ህጉ ውስጥ ተመልክተው ስለምናገኛቸው ነው፡፡ እነዚህን

ምክንያቶች አንዳንድ ጊዜ ቅጣቱን ለማክበድ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ቅጣቱን ለማቅለል ሊውሉ እንደሚችሉ ከወንጀል ሕጉ የተለያዩ ድንጋጌዎች መረዳት እንችላለን፡፡

ለምሳሌ፣

1. የወንጀል አድራጊው ግላዊ የአደገኛነት መጠን (dangerous disposition of the criminal) በሚመለከት ወንጀሉን ያደረገው በከሀዲነት፣በተለየ ክፋት ወይም ጨካኝነት ከሆነ(84(1)(ሀ)፣ የወንጀል አፈጻጸም ሁኔታ በለሊት፣ በሽብር በጦር መሳሪያ ወዘተ የተለየ አደገኛነቱን አሳይቶ እንደሆነ 84(1)(ሐ) በማክበጃነት፣ ያጠፋው በየዋህነት ወይም ባልታሰበ ድንገተኛ አጋጣሚ እንደሆነ፣(82(1)(ሀ) በማቅለያነት ያገለግላል፡፡
2. የወንጀል አድራጊው ያለፈ የህይወት ታሪኩን በሚመለከት ቀድሞ ወንጀል አድርጎ የተቀጣ ከሆነ በማክበጃነት (አንቀጽ 84(1)(ሐ)፣ ቀድሞ ወንጀል ፈጽሞ ያልነበረና መልካም ጸባይ የነበረው ከሆነ በማቅለያነት (አንቀጽ 82(1)(ሀ) ያገለግላል፣
3. ያነሳሱትን ምክንያቶችና አላማ (motive and purpose) በተከበረና በግል ጥቅም ባልተመሰረተ ፍላጎት እንደሆነ(82(1)(ለ)፣ የተበደለው ሰው ከብርቱ ፈተና ላይ ጥሎት እንደሆነ፣82(1)(መ) በማቅለያነት፣ መጥፎ አመልን በሚያሳይ ምቀኝነት፣ ጥላቻ ወይም ስግብግብነት እንደሆነ 84(1)(ሀ) በማክበጃነት ያገለግላል፡፡
4. የግል ኑሮውን ሁኔታ (personal circumstance) (በአንቀጽ 90(2) መቀጮ ለመጣል ሊታዩ የሚገባቸው የግል ኑሮው ሁኔታ ተዘርዝሮ እናገኛለን፡፡ የቤተሰቡ ሁኔታ፣ የገቢ ምንጩ ወዘተ የመቀጮውን መጠን ለመወሰን ያገለግላል፡፡
5. የትምህርቱን ደረጃ (standard of education) በእውቀት ማነስ፣ ባለማወቅ እንደሆነ (82(1)(ሀ) በማቅለያነት ያገለግላል፡፡
6. የአፈጻጸሙን ሁኔታ (circumstances of its commission) የተጣለበትን ሀላፊነት ያላግባብ በመገልገል እንደሆነ 84(1)(ለ) ፣ ወንጀሉን ያደረገው በቡድን ወይም ከሌሎች ጋር በመስማማት እንደሆነ 84(1)(መ) በማክበጃነት ያገለግላል፡፡

በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 189 እንደተመለከተው ዳኛው በቅድሚያ ማክበጃ ምክንያቶችን መሰረት አድርጎ እንደሚያከብድ ያስቀመጠ ስለሆነ፣ በማክበጃ ምክንያቶች መሰረትም ቅጣቱን ለማክበድ መጀመሪያ መነሻ ቅጣት ማስቀመጥ ስለሚያስፈልግ፣ መነሻ ቅጣቱ ሲወሰን ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች ከመታየታቸው በፊት የሚወሰን ነው ማለት ነው፡፡

ስለሆነም የወንጀል ደረጃዎችን ለማውጣት በወንጀል ህጉ 88 ያሉት ምክንያቶች ሁሉ ሳይሆን ታሳቢ የተደረጉት በአንድ ወይም በሌላ መልኩ በማክበጃነት ወይም በማቅለያነት ሊጠቀሱ የማይችሉ በአንቀጽ 88 የተመለከቱት ምክንያቶች ናቸው፡፡

ስለሆነም በአንቀጽ 88(2) ከተመለከቱት ቅጣቱን ለመወሰን ከግምት ሊገቡ ከሚገባቸው ምክንያቶች አንዱ የወንጀሉ ከባድነት የሚለው ሲሆን፣ የወንጀሉ ከባድነት ደግሞ ከየወንጀል አይነቱ ጋር እየተነጻጸረ የሚመዘን ስለሚሆን መመሪያው የወንጀል ደረጃዎችን ለማውጣት ቅድሚያ የሰጠው የወንጀል ደረጃውን ከወንጀሉ ከባድነት አንጻር ደረጃ በማውጣት ነው፡፡

ስለሆነም ጥፋት አድራጊው ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ድንጋጌ አንድ ቢሆንም፣ ከወንጀሉ ከባድነት አንጻር አንዱ ከሌላው የተለየ ከሆነ መነሻ ቅጣታቸውም ተመሳሳይ ሊሆን ስለማይገባው እንደወንጀሉ ከባድነት መነሻው ከዝቅተኛው ጀምሮ ከፍ እያለ ሊሄድ ይገባል የሚል መነሻ አለው፡፡ በዚህ መሰረትም በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ለተወሰኑት ወንጀሎች የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተውላቸዋል፡፡

የቅጣት አወሳሰን መመሪያው ደረጃ ላልተዘጋጀላቸው ወንጀሎች ወደፊት በዝርዝር ደረጃ በደረጃ የሚዘጋጅ መሆኑን በማስቀመጥ ይሁንና ዝርዝር የወንጀል ደረጃ ባይዘጋጅላቸውም ቅጣቱን ለመወሰን ደረጃ እንዴት ሊወጣላቸው እንደሚገባ አጠቃላይ መመሪያዎችን ይዞ የተዘጋጀ ነው፡፡ ስለሆነም በእነዚህ መመሪያዎች መሰረት ደረጃዎች እንደሚወጡ ያስቀምጣል፡፡

## 4.2. ለእያንዳንዱ የወንጀል ደረጃ የመነሻ ቅጣት አወሳሰን፣

### 4.2.1. ለዝቅተኛውና ከፍተኛው የወንጀል ደረጃ የመነሻ ቅጣት አወሳሰን

1. ለእያንዳንዱ የወንጀል ደረጃ የመነሻ ቅጣት ለመወሰን መመሪያው ህግ አውጪው ለእያንዳንዱ የወንጀል ድርጊት የቅጣት መነሻና ጣሪያ አድርጎ ያስቀመጣቸው የቅጣት መጠኖች ትርጉም ሊኖራቸው በሚችል መልኩም የቅጣት መመሪያው መዘጋጀት አለበት የሚል መነሻ አለው፡፡ ማለትም በወንጀል አፈጻጸሙም ሆነ ከባድነቱ ቀላልና ዝቅተኛ የሚባለው የቅጣቱ መነሻ በወንጀል ህጉ የተቀመጠው መነሻ መሆን አለበት የሚል መነሻ አለው፡፡ ለምሳሌ ቅጣቱ ከ1 አመት ቀላል እስራት እስከ 5 አመት ጽኑ እስራት የሚል

ከሆነ፣ ድንጋጌውን በመጣስ ከሚፈጸመው ወንጀል በተነጻጻሪ ቀላልና ዝቅተኛ የሚባለው የወንጀል ድርጊት መነሻ ቅጣቱ 1 አመት ቀላል እስራት መሆን አለበት የሚል ነው። ስለሆነም ለእያንዳንዱ የወንጀል ድንጋጌ ዝቅተኛ ደረጃ በወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል የተቀመጠው ዝቅተኛ መነሻ እንዲሆን ተደርጎ የተዘጋጀ ነው።

2. በወንጀል ድንጋጌው ውስጥ ለሚወድቀው ከፍተኛ የወንጀል ደረጃ ለድንጋጌው የተመለከተው ጣሪያ ላይ አይደርስም። ምክንያቱም በልዩ ክፍል የተመለከቱት የቅጣት ጣሪያ ላይ የሚደረሰው ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃዎች ሲኖሩ ነው። የወንጀል ህግ ቁጥር 183 ቅጣቱ እንዲከብድ ህጉ በደነገገ ጊዜ (84) ለቅጣቱ ማክበጃ የሆኑትን ምክንያቶች አይነትና ብዛት እንዲሁም ወንጀለኛው የፈጸመውን ጥፋት ከባድነት በማመዛዘን ፍርድ ቤቱ በዚህ ሕግ ልዩ ክፍል በተመለከተው አግባብነት ባለው ድንጋጌ ከተወሰነው ቅጣት ጣሪያ ሳያልፍ ቅጣቱን ይወስናል። ስለሆነም በህጉ አንቀጽ 84 የተመለከቱትን ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃዎች አምስት ሲሆኑ፣ ሁሉም ተማልተው ሲገኙ ጣሪያው ላይ እንዲደርስ ታሳቢ በማድረግ፣ ከአምስት እርከን በታች ለከፍተኛው ደረጃ መነሻ እንዲሆን ተደርጎአል።

<u>ምሳሌ 1</u>

<u>በስልጣን አለአግባብ መገልገል ወንጀል 407(1)</u>

- በወንጀል ሕግ 407(1) ውስጥ ለሚወድቁ የወንጀል ድርጊቶች 6 የወንጀል ደረጃዎች አሉት።
- ዝቅተኛው ወይም ደረጃ 1 መነሻው ቅጣት የቅጣት እርከን 7 ሲሆን፣ ይህም በወንጀል ህጉ ከተቀመጠው መነሻ አንድ አመት የሚነሳ ነው።
- ከፍተኛ ደረጃ የተባለው ደግሞ መነሻ ቅጣቱ በእርከን 23 የተቀመጠ ሲሆን፣ ይህም ከ 6 አመት እስከ 7 አመት ከ2 ወር ነው።
- በ407(1) ከፍተኛ ለተባለው የወንጀል ደረጃ 6 (እርከን 23) አምስት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ቢኖሩና ቅጣቱ በአምስት እርከን ቢከብድ እርከን 28 ላይ ይደርሳል።
- የእርከን 28 ቅጣት ከ9 አመት እስከ 10 አመት ከ10 ወር ነው። በወንጀል ህጉ ለወንጀሉ የተቀመጠው የቅጣት ጣሪያ 10 አመት ጽኑ እስራትን ያካተተ ነው።
- ስለሆነም በዚህ እርከን ውስጥ ከ10 አመት ሳይበልጥ ቅጣቱ ይወሰናል ማለት ነው።

**ምሳሌ 2**

**በስልጣን አለአግባብ መገልገል ወንጀል 407(2)**

- በወንጀል ሕግ 407(2) ውስጥ ለሚወድቁ የወንጀል ድርጊቶች 4 የወንጀል ደረጃዎች አሉት፡፡
- ዝቅተኛው ወይም ደረጃ 1 መነሻው ቅጣት የቅጣት እርከን 25 ሲሆን፣ ይህም በወንጀል ህጉ ከተቀመጠው መነሻ ሰባት አመት የሚነሳ ነው፡፡
- ከፍተኛ ደረጃ የተባለው ደረጃ 4 መነሻው የቅጣት እርከን 28 ሲሆን የዚህም የቅጣት መነሻ ከ9 አመት እስከ 10 አመት ከ10 ወር ነው፡፡
- በ407(2) ከፍተኛ ለተባለው የወንጀል ደረጃ 4 አምስት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ቢኖሩና ቅጣቱ በአምስት እርከን ቢከብድ እርከን 33 ላይ ይደርሳል፡፡
- የእርከን 33 ቅጣት ከ14 አመት እስከ 16 አመት ከ10 ወር ነው፡፡ በወንጀል ህጉ ለወንጀሉ የተቀመጠው የቅጣት ጣሪያ 15 አመት ጽኑ እስራትን ያካተተ ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ እርከን ውስጥ ከ15 አመት ሳይበልጥ ቅጣቱ ይወሰናል ማለት ነው፡፡

**ምሳሌ 3**

**ከባድ ስርቆት 669**

- በወንጀል ሕግ 669 ውስጥ ለሚወድቁ የወንጀል ድርጊቶች 9 የወንጀል ደረጃዎች አሉት፡፡
- ዝቅተኛው ወይም ደረጃ 1 መነሻው ቅጣት የቅጣት እርከን 7 ሲሆን፣ ይህም በወንጀል ህጉ ከተቀመጠው መነሻ 1 አመት የሚነሳ ነው፡፡
- ከፍተኛ ደረጃ የተባለው ደረጃ 9 መነሻው የቅጣት እርከን 27 ሲሆን የዚህም የቅጣት መነሻ ከ8 አመት ከ5 ወር እስከ 10 አመት ነው፡፡
- በ669 ከፍተኛ ለተባለው የወንጀል ደረጃ 9 (እርከን 27) አምስት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ቢኖሩና ቅጣቱ በአምስት እርከን ቢከብድ እርከን 32 ላይ ይደርሳል፡፡
- የእርከን 32 ቅጣት ከ13 አመት እስከ 15 አመት ከ8 ወር ነው፡፡ በወንጀል ህጉ ለወንጀሉ የተቀመጠው የቅጣት ጣሪያ 15 አመት ጽኑ እስራትን ያካተተ ነው፡፡
- ስለሆነም በዚህ እርከን ውስጥ ከ5 አመት ሳይበልጥ ቅጣቱ ይወሰናል ማለት ነው፡፡

## 4.2.2. በድንጋጌው ዝቅተኛ የወንጀል ደረጃና ከፍተኛ የወንጀል ደረጃ መካከል ያሉትን የወንጀል ደረጃዎች መነሻ ቅጣት አወሳሰን

በድንጋጌው ዝቅተኛው የወንጀል ደረጃና ከፍተኛው የወንጀል ደረጃ የሚያርፉበት ከታወቀ፣ በእነዚህ መሀከል ያሉት የተለያዩ የወንጀል ደረጃዎች በቁጥራቸው ልክ ከመነሻው እስከ መድረሻው ያለውን የቅጣት ዘመን በማካፈል የቅጣት መነሻቸው ተወስኗል፡፡

**ምሳሌ 1፣**

በ407(1) ስድስት የወንጀል ደረጃዎች አሉ፡፡

- ዝቅተኛው ደረጃ መነሻው አንድ አመት ስለሆነ እርከን 7 ላይ ነው፡፡
- ከፍተኛው ደረጃ 6 ደግሞ እርከን 23 ላይ ነው፡፡
- በመካከላቸው 16 እርከን ልዩነት አለ፡፡

ስለሆነም 16 እርከን ለ5 ሲካፈል (የመነሻው የታወቀ ስለሆነ አንድ ይቀንሳል) የሚገኘው ውጤት 3 አካባቢ ነው፡፡ ስለሆነም ከዝቅተኛው ጀምሮ ለእያንዳንዱ 3 እርከን እያለፈ መነሻ ቅጣቱ ተቀምጧል፡፡ በማጠጋጋት አንዱን 4 እርከን ልዩነት እንዲኖረው ተደርገል፡፡

**ምሳሌ 2፣**

በ665 7 የወንጀል ደረጃዎች አሉ፡፡

- ዝቅተኛው ደረጃ መነሻው አንድ 10 ቀን ስለሆነ እርከን 2 ላይ ነው፡፡
- ከፍተኛው ደረጃ 2 ደግሞ እርከን 14 ላይ ነው፡፡
- በመካከላቸው 12 እርከን ልዩነት አለ፡፡

ስለሆነም 12 እርከን ለ6 ሲካፈል የሚገኘው ውጤት 2 ነው፡፡ ስለሆነም ከዝቅተኛው ጀምሮ ለእያንዳንዱ 2 እርከን እያለፈ መነሻ ቅጣቱ ተቀምጧል፡፡

### 4.2.3. የገንዘብ መቀጮን በተመለከተ የቅጣት ጣሪያው የተወሰነበት ሁኔታ፣

የገንዘብ መቀጮውን በተመለከተ ለወንጀሉ ድርጊት ከተቀመጠው ጣሪያ ሳይበልጥ በድንጋጌው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ወንጀል አድራጊ እስከመቀጮው ጣሪያ እንዲከፍል በሚያደርግ

መልኩ፣የወንጀል ደረጃው ዝቅ እያለ በሄደ ቁጥርም የገንዘብ መቀጮ ጣሪያውም በዚያው መልክ በአንድ እርከን እየቀነሰ እንዲሄድ በማድረግ ደረጃው ተዘጋጅቷል።

**ምሳሌ**

በ407(1) ከፍተኛው የገንዘብ መቀጮ ብር 10000 ነው።

- ስለሆነም ከፍተኛው ደረጃ 6 ሲሆን ለዚህ መቀጮው እርከን 6 ነው። (10000)
- የወንጀል ደረጃው ደረጃ 5 ከሆነ የመቀጮው እርከን 5 ነው። (7000)

በዚህ መልኩ በሁሉም መቀጮ በሚያስቀጡ የወንጀል ድርጊቶች የመቀጮው ጣሪያ የሚያርፍበት እርከን ተለይቷል።

## 4.3. ደረጃ ለወጣላቸው ወንጀሎች ቅጣት አወሳሰን ዝርዝር አሰራር ማሳያ

**ቅጣቱ የሚወሰንበት ቅደም ተከተል**

1. ጥፋተኛ ተብሎ ሲወሰን ጥፋተኛ ተብሎ የተወሰነበት ድንጋጌም የሚታወቅ ስለሆነ፣ ለወንጀሉ ከወጡት የወንጀል ደረጃዎች አንጻር ደረጃው ይለያል።
2. ለወንጀል ደረጃው የተቀመጠው የቅጣት እርከን ይለያል።
3. በእርከኑ ውስጥ ዳኛው ቅጣቱን ይወስናል።

### 4.3.1. በስልጣን አለአግባብ መገልገል የሚፈጸም ወንጀልን በተመለከተ፣

በመመሪያው መሰረት ዳኛው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 407 የወንጀል ደረጃውን ለመወሰን ከግምት የሚያስገባቸው ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው። እነርሱም፣ የአጥፊው የስልጣን ደረጃ፣ በወንጀሉ ምክንያት የደረሰ ጥቅም ወይም ጉዳት እና ወንጀሉ የተፈጸመበት አላማ ናቸው። እነዚህ መስፈርቶች ቅጣቱን ለማክበድ እንደሚያገለግሉ በድንጋጌው ንኡስ አንቀጽ 2 ውስጥ የተደነገጉ ስለሆነ ደረጃውን ለማውጣት በመስፈርትነት እንዲያገለግሉ ተደርገዋል።

**ምሳሌ 1.**

በ407(1) መሰረት ጥፋተኛ የተባለው ሰው የስልጣን ደረጃው የመምሪያ ሀላፊ ሲሆን፣ በወንጀሉ ምክንያት ያገኘው የማይገባ ጥቅም 30000 ብር ነው።

በቅድሚያ የወንጀል ደረጃው እንደሚከተለው ይለያል፡፡

- የመጀመሪያው ጥያቄ የስልጣን ደረጃው ምንድነው የሚል ነው፡፡ የስራ ሀላፊነቱ የመምሪያ ሀላፊ ስለሆነ **መካከለኛ ባለስልጣን** በሚለው ላይ ይወድቃል፡፡
- የተገኘው ጥቅም ብር 30000 ስለሆነ መካከለኛ ጥቅም ወይም ጉዳት በሚለው ስር ይወድቃል፡፡ (ተከሳሽ በወንጀሉ ምክንያት ያገኘውን ጥቅም በገንዘብ ተምኖ ማስቀመጥ የማይቻል ከሆነ **ዝቅተኛ ጥቅም** በሚለው ካታጎሪ ውስጥ ይወድቃል፡፡)
- በሶስተኛ ደረጃ የሚጠየቀውና የሚጣራው ወንጀሉን የፈጸመው በምን አላማ ነው የሚለው ነው፡፡ በመመሪያው መሰረት ሁለት መስፈርቶች አሉ፡፡ ወንጀሉን የፈጸመው በችግር ወይም በተጽእኖ ከሆነ ዝቅተኛው መደብ ውስጥ ሲወድቅ ከዚህ ውጭ ከሆነ ከባድ አላማ በሚለው ውስጥ ይወድቃል ማለት ነው፡፡
- በመመሪያው እንደተመለከተው ወንጀሉን የፈጸመው በችግር ወይም በተጽአኖ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ከሌለ ከባድ አላማ እንዳለ እንደሚቆጠር ተመልክቷል፡፡
- በዚህ ጉዳይ ወንጀል አድራጊው በችግር ወይም በተጽእኖ ወንጀሉን ለመፈጸሙ የሚያስረዳ ማስረጃ የለም፡፡ ስለሆነም የተፈጸመበት አላማ **ከባድ አላማ** ነው ማለት ነው፡፡

ከእነዚህ በመነሳት (መካከለኛ ስልጣን/ መካከለኛ ጥቅም ወይም ጉዳት/ በከባድ አላማ) የወንጀል ደረጃውን በመመሪያው ከተያያዘው አባሪ ሶስት ስንፈልግ በወንጀል ደረጃ 6 ውስጥ እንደሚወድቅ ይታወቃል ማለት ነው፡፡

**መነሻ ቅጣቱን መወሰን፣**

**የእስራት ቅጣትን መወሰን፣**

- የወንጀል ደረጃ 6- እስራትን በተመለከተ ቅጣቱ የሚወድቀው እርከን 23 ላይ እንደሆነ በአባሪ ሶስት አራተኛው ኮለም (አምድ) ላይ ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም የቅጣት እርከኑ ተለየ ማለት ነው፡፡
- በእርከን 23 የቅጣት ሬንጅ (ፍቅድ ስልጣን) ከ 6 አመት እስከ 7 አመት ከ2 ወር ነው፡፡
- ዳኛው በዚህ ሬንጅ ውስጥ የተለያዩ የወንጀሉን ልዩ ባህርዮች በመመዘን ቅጣቱን ይወስናል፡፡ በዚህ ጉዳይ ቅጣቱን ለምሳሌ 6 አመት ብሎ መነሻ ቅጣቱን ሊወስን ይችላል፡፡

**<u>የገንዘብ መቀጮን በተመለከተ፣</u>**

- ለ407(1) የወንጀል ደረጃ 6 በአባሪ ሶስት የተመለከተው የመቀጮው እርከን 6 ነው፡፡
- የመቀጮ እርከን 6 ጣሪያው እስከ ብር 10000 ድረስ ነው፡፡
- ዳኛው ከዚህ ጣሪያ ሳያልፍ ቅጣቱን ይወስናል ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ብር 8000 ብሎ ሊወስን ይችላል፡፡
- ይሁንና መቀጮ ሲወሰን ታሳቢ የሚደረጉ በርካታ ምክንያቶች ያሉ ስለሆነ መቀጮውን ላይወስንም ይችላል፡፡

**<u>የተፈጸመበት አላማ ከባድ ተብሎ በመመሪያው ከተጠቀሰውም በላይ በሆነ ጊዜ ቅጣቱ እንዴት ይወሰናል?</u>**

በመመሪያው እንደተመለከተው ወንጀል ፈጻሚው ወንጀሉን የፈጸመበት አላማ በመመሪያው ከባድ አላማ በሚል ከተገለጸውም በላይ ከባድ ስለመሆኑ ዳኛው የሚያምን ከሆነ ማለትም ለምሳሌ ወንጀሉ የተፈጸመው የሀገር ምስጢርን ለሌላ አገር ለማሳለፍ ከሆነ፣ በአንቀጽ 407 መሰረት የተፈጸመበት አላማ ቅጣቱን እንደሚያከብደው ያስቀመጠ ስለሆነ በ407(1) ውስጥ ይወድቅ የነበረው በ407(2) ውስጥ ይወድቃል ማለት ነው፡፡

በ407(2) ውስጥ የነበረው ከአንድ በላይ ማክበጃ ምክንያቶች ተሟልተው የሚገኙበት ስለሆነ አላማው ከባድ አላማ ከተባለውም በላይ ከሆነ ከአንድ በላይ ማክበጃ ተደራርበው ስለሚገኙ በ407(3) ውስጥ ይወድቃል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የወንጀል ደረጃው ከዚህ በታች በተመለከተው መሰረት ይስተካከላል ማለት ነው፡፡

- የስልጣን ደረጃው ዝቅተኛ/ የተገኘው የጥቅም መጠን ዝቅተኛ/ የተፈጸመበት አላማ ከባድ አላማ ከተባለው በላይ ከሆነ በአንቀጽ 407(2) የወንጀል ደረጃ 7 ይሆናል፡፡
- የስልጣን ደረጃው መካከለኛ/የተገኘው ጥቅም መጠን ዝቅተኛ/ የተፈጸመበት አላማ ከባድ አላማ ከተባለው በላይ ከሆነ በአንቀጽ 407(2) የወንጀል ደረጃ 8 ይሆናል፡፡

- የስልጣን ደረጃው ዝቅተኛ/ የተገኘው የገንዘብ መጠን መካከለኛ ከሆነ/ የተፈጸመበት አላማ ከባድ አላማ ከተባለው በላይ ከሆነ በአንቀጽ 407(2) የወንጀል ደረጃ 9 ይሆናል፡፡
- የስልጣን ደረጃው መካከለኛ/የተገኘው ጥቅምም መካከለኛ ከሆነ/ የተፈጸመበት አላማ ከባድ አላማ ከተባለው በላይ ከሆነ በአንቀጽ 407(2) የወንጀል ደረጃ 10 ይሆናል፡፡
- በ407(2) በደረጃ 1 እና 2 ውስጥ የሚወድቀው ከአላማው አንጻር ሌላ ተደራቢ ማክበጃ ምክንያት በመኖሩ በ407(3) ደረጃ 11 ውስጥ የሚወድቅ ይሆናል፡፡
- በ407(2) በደረጃ 3 እና 4 ውስጥ የሚወድቀው ደግሞ ከአላማው አንጻር ሌላ ተደራቢ ማክበጃ ምክንያት በመኖሩ በ407(3) ደረጃ 12 ውስጥ የሚወድቅ ይሆናል፡፡[13]

**<u>ምሳሌ 1</u>**

ከዚህ በላይ በ407(1) የወንጀል ደረጃ 6 ላይ የወደቀውን ምሳሌ ወስደን ወንጀሉ የተፈጸመበትን አላማ እየቀያየርን እንመልከት፣

- ጥፋተኛ የተባለው ሰው የስልጣን ደረጃው የመምሪያ ሀላፊ ነው፡፡ (መካከለኛ ስልጣን)
- በወንጀሉ ምክንያት ያገኘው የማይገባ ጥቅም 30000 ብር ነው፡፡ (መካከለኛ ጥቅም)
- ወንጀሉን የፈጸመው <u>በችግር</u> ነው፡፡ (በችግር)

እነዚህ ሶስቱ መስፈርቶች ተሟልተው የሚገኙት በአባሪ ሶስት በ407(1) በወንጀል ደረጃ 5 ነው፡፡

**<u>ወንጀሉ የተፈጸመው በአፍቅሮ ንዋይ ከሆነስ?</u>**

[13] በመመሪያው አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 6 ከ‹ሀ› እስከ ‹ሠ› ደረጃ 7፣8፣9፣10፣11 እና 12 በሚል የተጠቀሱት የቁጥር ስህተት ነው፡፡ ስለሆነም
- ደረጃ 7 (407(2) ደረጃ 1)፣
- ደረጃ 8 (407(2) ደረጃ 2)፣
- ደረጃ 9 (407(2) ደረጃ 3)፣
- ደረጃ 10 (407(2) ደረጃ 4)፣
- ደረጃ 11 (407(3) ደረጃ 1)፣
- ደረጃ 12 (407(3) ደረጃ 2

ተብለው ሊነበቡ ይገባል፡፡

በችግር የሚለው ተቀይሮ ከባድ አላማ ይሆናል፡፡ ስለሆነም አሁን (መካከለኛ ስልጣን/መካከለኛ ጥቅም/ <u>ከባድ አላማ</u>) ነው፡፡ እነዚህ ሶስት መስፈርቶች ተሟልተው የምናገኘው ደግሞ በአባሪ ሶስት በ407(1) በወንጀል ደረጃ 6 ነው፡፡

<u>ወንጀሉ የተፈጸመው የአገርን ምስጢር ለሌላ ባእድ ለማሳለፍ ከሆነስ?</u>

(መካከለኛ ስልጣን/መካከለኛ ጥቅም/ከባድ አላማ በላይ)

በዚህ መሰረት ወንጀሉን በማክበድ ከንኡስ ቁጥር አንድ ወደንኡስ ቁጥር ሁለት የሚያሳድግ አንድ ማክበጃ ምክንያት ስለተሟላ በመመሪያው በተመለከተው መሰረት በ407(2) የወንጀል ደረጃ 3 ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይህም ለእስራቱ በእርከን 27፣ ለመቀጮው በእርከን 9 ላይ ይወድቃል ማለት ነው፡፡

<u>ምሳሌ 2</u>

ከዚህ በላይ ያለውን ምሳሌ ወስደን ከስልጣን ደረጃው አንጻር ወይም ከተገኘው ጥቅም አንጻር ከፍተኛ የሚባለው ውስጥ የሚገባ እንደሆነ አድርገን ብንወስደው የሚከተለው ውጤት ይመጣል፡፡

- ጥፋተኛ የተባለው ሰው የስልጣን ደረጃው ሚኒስትር ነው፡፡ (ከፍተኛ ስልጣን)
- በወንጀሉ ምክንያት ያገኘው የማይገባ ጥቅም 30000 ብር ነው፡፡ (መካከለኛ ጥቅም)
- ወንጀሉን የፈጸመው <u>በችግር</u> ነው፡፡ (በችግር)

እነዚህ ሶስቱ መስፈርቶች ተሟልተው የሚገኙት በአባሪ ሶስት በ407(2) በወንጀል ደረጃ 3 ነው፡፡ የእስራት ቅጣት እርከኑ 27 ሲሆን የመቀጮው እርከን 9 ነው፡፡

<u>ወንጀሉ የተፈጸመው በአፍቅሮ ንዋይ ከሆነስ?</u>

በችግር የሚለው ተቀይሮ ከባድ አላማ ይሆናል፡፡ ስለሆነም አሁን (ከፍተኛ ስልጣን/መካከለኛ ጥቅም/ <u>ከባድ አላማ</u>) ነው፡፡ እነዚህ ሶስት መስፈርቶች ተሟልተው የምናገኘው ደግሞ በአባሪ ሶስት በ407(2) በወንጀል ደረጃ 4 ነው፡፡ የእስራት ቅጣት እርከኑ 28 ሲሆን የመቀጮው እርከን 10 ነው፡፡

<u>ወንጀሉ የተፈጸመው የአገርን ምስጢር ለሌላ ባእድ ለማሳለፍ ከሆነስ?</u>

(ከፍተኛ ስልጣን/መካከለኛ ጥቅም/ከባድ አላማ በላይ)

በዚህ መሰረት ወንጀሉን በማክበድ ከንኡስ ቁጥር ሁለት ወደንኡስ ቁጥር ሶስት የሚያሳድግ ከአንድ በላይ ማክበጃ ምክንያት ስለተሟላ በመመሪያው በተመለከተው መሰረት በ407(3) የወንጀል ደረጃ 2 ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይህም ለእስራቱ በእርከን 32፣ ለመቀጮው በእርከን 12 ላይ ይወድቃል ማለት ነው፡፡

<u>4.3.2. በሰው አካልና ጤንነት ላይ የሚፈጸም ወንጀልን በተመለከተ፣</u>

በሰው አካልና ጤንነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተመለከተ የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ከ555-560 ድረስ ናቸው፡፡ እነዚህ ቀላል የአካል ጉዳት እና ከባድ የአካል ጉዳት በሚል የተከፈሉ ናቸው፡፡

1. <u>በ555 መሰረት ጥፋተኛ ነው ተብሎ በተወሰነበት ሰው ላይ የቅጣት አወሳሰን፣</u>

በመመሪያው መሰረት ቅጣቱን ለመወሰን ዳኛው ከግምት የሚያስገባው የደረሰው የጉዳት መጠንን እና አጥፊው የሙያ ግዴታ ያለበት መሆኑን መሰረት ባደረገ መልኩ ነው፡፡ ስለሆነም የደረሰው ጉዳት፣ 1) ሊድን የሚችል ነው? 2) ዘላቂ የማይጠፋ ነው? 3) ለህይወቱ ያሰጋዋል? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሹን ያስቀምጣል፡፡

<u>ምሳሌ</u>

- በቀረበው ጉዳይ ላይ በወንጀል ሰለባው ላይ የደረሰው ጉዳት <u>ለህይወቱ የሚያሰጋ ነው</u>፡፡
- ወንጀል አድራጊው <u>ሙያዊ ግዴታ እንዳለበት</u> ተረጋግጧል፡፡

ስለሆነም ወንጀለኛው ያደረሰው ጉዳት 1) ለህይወቱ የሚያሰጋ ነው እንዲሁም 2) ሙያዊ ግዴታ ያለበት ነው፡፡

- እነዚህን ሁለት መስፈርቶች ያሟላ የወንጀል ደረጃ 7 ነው፡፡
- የእስራት ቅጣቱን ለመወሰን ደረጃ 7 በእርከን 27 ላይ ይወድቃል፡፡
- በእርከን 27 ላይ የቅጣት መነሻና መድረሻው ከ8 አመት ከ5 ወር እስከ 10 አመት ነው፡፡
- ዳኛው በዚህ እርከን ውስጥ ቅጣቱን ይወስናል ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ 9 አመት በሚል ሊወስን ይችላል፡፡

እነዚህ መስፈርቶች በተመሳሳይ በ558 እንዲሁም በ559 መሰረት ቅጣት ለመጣል የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ በመካከላቸው ያለው ልዩነት የወንጀል አድራጊው የሞራላዊ ሁኔታ ብቻ በመሆኑ ነው፡፡

<u>በ555/557 መሰረት የቅጣት አወሳሰን፣</u>

አንቀጽ 557 ንኡስ አንቀጽ 1 በጥቅሉ ማቅለያ ነው፡፡

ስለሆነም በ557 (1) ከተመለከቱት ማቅለያዎች ተሟልተው ከሆነ ዳኛው ቅጣቱን ለመወሰን በሰንጠረዡ ወደተቀመጠው መስፈርት መሄድ ብቻ ነው የሚያስፈልገው፡፡

የወንጀል ደረጃዎቹ ተመሳሳይ ናቸው፡፡ የቅጣት እርከኑን ለመወሰን ብቻ ነው ወደ557 የሚሄደው፡፡

ስለሆነም በአንቀጽ 555 መሰረት ጥፋተኛ የሆነ ነገር ግን በ557 መሰረት ማቅለያ የሚኖረው ከሆነ የቅጣት መጠኑ አወሳሰን ከዚህ በላይ ከተመለከትነው ምሳሌ አንጻር እንደሚከተለው ነው፡፡

- የደረሰው ጉዳት <u>ለህይወቱ የሚያሰጋ ከሆነ</u> እና <u>ሙያዊ ግዴታ እያለበት ከሆነ</u> የወንጀል ደረጃው 7 ነው፡፡
- ለአንቀጽ 55ሰ/557 ደረጃ 7 የሚወድቅበት የእስራት ቅጣት እርከን 11 ለመቀጮ ደግሞ እርከን 4 ነው፡፡
- እርከን 11 ቅጣቱ ከ1 አመት ከ8 ወር እስከ 2 አመት ከ2 ወር ነው፡፡ ዳኛው በዚህ ውስጥ ይወስናል ማለት ነው፡፡
- የመቀጮ እርከን 4 ጣሪያው እስከ ብር 5000 ነው፡፡ ስለሆነም ዳኛው ከዚህ ባልበለጠ መቀጮውን ይወስናል ማለት ነው፡፡

በ557 ውስጥ ያሉት ማቅለያዎች ቢኖሩም በንኡስ አንቀጽ 2 በተመለከተው መሰረት ተጎጂው ፈቃዱን ቢሰጥም ተጎጂው እሺታውን የሰጠው የሚያስከትለውን ውጤት የማይረዳ መሆኑን መረዳት ከተቻለ በ557(1) መሰረት ከተደረሰበት የቅጣት እርከን 7 በመጨመር ቅጣቱ ይወሰናል፡፡ በዚህ መሰረትም

1. ደረጃ 1 የቅጣት እርከኑ 5 (ከ6 ወር-9 ወር) የነበረው የቅጣት እርከኑ 12 (ከ2 አመት-2 አመት ከ6ወር) ይሆናል፡፡
2. ደረጃ 2 የቅጣት እርከኑ 6 (ከ8ወር- 1 አመት ) የነበረው የቅጣት እርከኑ 13 (ከ2 አመት ከ3 ወር-2 አመት ከ9 ወር) ይሆናል፡፡

3. ደረጃ 3 የቅጣት እርከኑ 7 (ከ1 አመት-1 አመት ከ3 ወር) የነበረው የቅጣት እርከኑ 14 (ከ2 አመት ከ6 ወር- 3 አመት ይሆናል።
4. ደረጃ 4 የቅጣት እርከኑ 8 (ከ1 አመት ከ2 ወር -1 አመት ከ6 ወር) የነበረው የቅጣት እርከኑ 15 (ከ2 አመት ከ9 ወር-3 አመት ከ3 ወር ይሆናል)
5. ደረጃ 5 የቅጣት እርከኑ 9(ከ1 አመት ከ4 ወር-1 አመት ከ8 ወር) የነበረው የቅጣት እርከኑ 16 (ከ3 አመት-3 አመት ከ7 ወር ይሆናል)
6. ደረጃ 6 የቅጣት እርከኑ 10 ( ከ1 አመት ከ6 ወር-1 አመት ከ10 ወር) የነበረው የቅጣት እርከኑ 17 (ከ3 አመት ከ3 ወር-3 አመት ከ11 ወር ይሆናል።
7. ደረጃ 7 የቅጣት እርከኑ 11 (ከ1 አመት ከ8 ወር-2 አመት ከ2 ወር) የነበረው የቅጣት እርከኑ 18 (ከ3 አመት ከ7 ወር-4 አመት ከ4 ወር) ይሆናል። ይሁንና ተጨማሪው 4 ወር በህጉ ከተቀመጠው ጣሪያ በላይ ስለሆነ ቅጣቱ ከ4 አመት አይበልጥም ማለት ነው።

2. <u>በአንቀጽ 556 መሰረት ቅጣት የሚወሰንበት ሁኔታ፣</u>

በወንጀል ህጉ 556 መሰረት ቅጣቱን ለመወሰን ዳኛው ከግምት የሚያስገባቸው የሚከተሉትን ነው።

1. የደረሰው ጉዳት በ555 በተመለከተው መስፈርት ውስጥ የማይወድቅ ከሆነ ቀላል ጉዳት ስለሚሆን በ556(1) መሰረት ቅጣቱ ይወሰናል። ይህም በሰንጠረዡ ለ556 የወንጀል ደረጃ 1 የተባለው ሲሆን የእስራት ቅጣት እርከኑ 2 (ከ10 ቀን-- 3 ወር) ሲሆን፣ የመቀጮ እርከኑ ደግሞ 3 እስከ ብር 3000 በሚደርስ ይቀጣል ማለት ነው።

ይሁንና የደረሰው ጉዳት ቀላል ቢሆንም፣ በድንጋጌው በንኡስ አንቀጽ 2 ቅጣቱን ለማክበድ የሚያስችሉ ማክበጃ ምክንያቶች ተሟልተው ተገኝተው ከሆነ የቅጣት አወሳሰኑ በሚከተለው መልኩ ይሆናል።

1. በ556(2) መሰረት ቅጣቱን ለመወሰን ታሳቢ የሚደረጉት የሚከተሉት መስፈርቶች ናቸው። 1) ጉዳት ለማድረስ መሳሪያ መጠቀም አለመጠቀሙ፣ 2) የሙያ ወይም ሌላ ግዴታን በመተላለፍ እንደሆነ፣ 3) ተጎጂው በሽተኛ፣ ደካማ ወይም ራሱን መከላከል የማይችል እንደሆነ ናቸው።

2. ከእነዚህ ምክንያቶች አንዱ ብቻ ከተሟላ አንድ ማክበጃ፣ ሁለት ከተሟላ ሁለት ማክበጃ እያለ እንደተደራረቡት ማክበጃ ምክንያቶች ብዛት ደረጃውን በሚያሳድግ መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡

<u>ምሳሌ</u>

1. ወንጀል አድራጊው መሳሪያ ተጠቅሟል፡፡
2. ተጎጂው በሽተኛ ወይም ራሱን መከላከል የማይችል ነው፡፡
3. ወንጀል አድራጊው የሙያ ግዴታ የለበትም፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረበው ማስረጃ መረዳት የሚቻለው ሁለቱ ማክበጃዎች የተሟሉ መሆኑን ነው፡፡ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ ድርጊቱ የሚወድቀው በወንጀል ደረጃ 3 ላይ ነው፡፡

- የወንጀል ደረጃ 3ትን በተመለከተ የተቀመጠው የእስራት ቅጣት እርከን 7 ሲሆን፣ ለገንዘብ መቀጮው እርከን 5 ነው፡፡
- እርከን 7 ቅጣቱ ከ1 አመት እስከ 1 አመት ከሶስት ወር ነው፡፡ ስለሆነም ዳኛው በዚህ ሬንጅ ወይም ፍቅድ ስልጣን ውስጥ ቅጣቱን ይወስናል ማለት ነው፡፡
- የገንዘብ መቀጮውን በተመለከተ እርከን 5 እስከ ብር 7000 ድረስ ነው፡፡ ስለሆነም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 90 መሰረት ያሉትን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ ከብር 7000 ሳይበልጥ መቀጮውን ይወስናል ማለት ነው፡፡

### <u>4.3.3. የስርቆት ወንጀልን በሚመለከት የቅጣት አወሳሰን</u>

የስርቆት ወንጀልን በሚመለከት በ665 እና በ669 መሰረት የተለያዩ መስፈርቶች ቅጣቱን ለመወሰን ይውላሉ፡፡

1. <u>በ665 መሰረት ቅጣት አወሳሰን</u>

በ665 መሰረት ጥፋተኛ የተባለ ከሆነ፣ ደረጃውን ለመወሰን ከግምት የሚገባው በስርቆት ወንጀሉ የተገኘው ጥቅም መጠን ነው፡፡[14] ከዚህ አንጻር ደረጃው ይወሰናል ማለት ነው፡፡ በዚህ

---

[14] በዚህና በሌሎችም ደረጃውን ለመወሰን የገንዘብ መጠኑ ታሳቢ በተደረገባቸው በሁለት ተከታታይ ደረጃዎች መካከል ተመሳሳይ የገንዘብ መጠን ተመልክቷል፡፡ (ለምሳሌ ከብር 100-1000 እና ከብር 1000-2000)፡፡ በዚህ ውስጥ ብር 1000 የትኛው ደረጃ ውስጥ ይወድቃል የሚለው ያከራክራል፡፡ መመሪያው ሲዘጋጅ ታስቦ የነበረው ከብር 1000 በላይ ወዘተ በማለት ነው፡፡ ይህ በመመሪያው የተለያዩ አንቀጾች ተንጸባርቆ ይታያል፡፡ ለምሳሌ በመመሪያው አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 3 ከሙ-ረ ያለው አቀማመጥ ይህንን ያመለክታል፡፡ እንዲሁም በመመሪያው አባሪ ሶስት የመጨረሻው ደረጃ (ከ-በላይ) እያለ ያስቀምጣል፡፡ ለምሳሌ ለ665 ደረጃ 7 ከብር 100000 በላይ በማለት ነው የሚያስቀምጠው፡፡ ስለሆነም በዚሁ መሰረት ተረድቶ መመሪያው ተግባራዊ እንዲደረግ ይመከራል፡፡

መሰረት ደረጃው ሲወጣ የገንዘብ መጠኑ እስከ ብር 100 ከሆነ በደንብ መተላለፍ የሚታይ ስለሚሆን በዚህ ድንጋጌ ውስጥ አይወድቅም ማለት ነው፡፡[15]

**<u>ምሳሌ</u>**

በወንጀሉ የተሰረቀው ንብረት ግምት 500 ብር ነው፡፡

1. ብር 500 ከብር 1000 በታች ስለሆነ የወንጀል ደረጃው 1 ነው፡፡
2. ለ665 የወንጀል ደረጃ 1 የቅጣት እርከኑ 2 ይሆናል፡፡ የቅጣት እርከን ሁለት ቅጣቱ ከ10 ቀን-3 ወራት ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ዳኛው ቅጣቱን ይወስናል፡፡
3. ይህንን ወደግዴታ ስራ ወይም ወደመቀጮ ሊቀይረው ይችላል፡፡ ወደግዴታ ስራ ሲቀየር አንድ ቀን እስራት ከአንድ ቀን የግዴታ ስራ (8 ሰአት ጋር) እኩል ነው፡፡ መቀጮው ደግሞ እስከ ብር 500 ድረስ ነው፡፡
4. የገንዘብ መጠኑ ከብር 1000 በላይ እስከ ብር 2000 ከሆነ ደግሞ የወንጀል ደረጃው 2 የቅጣት እርከኑ 4 ይሆናል፡፡
5. የቅጣት እርከን 4 የቅጣት መነሻው ከ4 ወር-7 ወር ነው፡፡
6. ወዘተ

ይሁንና በስርቆት ከተገኘው የገንዘብ መጠን በተጨማሪ የስርቆት ወንጀሉ፣

1. ወንጀል በተፈጸመበት ሰው የእለት ኑሮ ወይም የድርጅቱ ስራ አደጋ ላይ ከወደቀ ከተቀመጠው እርከን በ2 ደረጃ ያድጋል፡፡ በዚህም መሰረት፣
   - የወንጀል ደረጃው 1 ለሆነው የቅጣት እርከኑ 2 መሆኑ ቀርቶ 4 ይሆናል፡፡
   - የወንጀል ደረጃው 2 ለሆነው የቅጣት እርከኑ 4 መሆኑ ቀርቶ 6 ይሆናል ማለት ነው፡፡
   - ወዘተ…
2. የተሰረቀው ንብረት ፈንጂ ተቀጣጣይ ነገር ከሆነ በተመሳሳይ እርከኑ በ2 ደረጃ ያድጋል፡፡ በዚህም መሰረት፣
   - የወንጀል ደረጃው 1 ለሆነው የቅጣት እርከኑ 2 መሆኑ ቀርቶ 4 ይሆናል፡፡
   - የወንጀል ደረጃው 2 ለሆነው የቅጣት እርከኑ 4 መሆኑ ቀርቶ 6 ይሆናል ማለት ነው፡፡

---

[15] በአንቀጽ 665(3) እጅግ አነስተኛ ግምት ያለው የሌላ ሰው እቃ ሲሆን በደንብ መተላለፍ ይቀጣል ስለሚል ይህንን መሰረት አድርጎ ነው እስከ መቶ ብር ድረስ በደንብ መተላለፍ ውስጥ የተካተተው፡፡

ወዘተ…

3. በዚህ መመሪያ መሰረት እነዚህ ቅጣቱን የሚያከብዱ ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ የሚያስጨምሩት የእርከን መጠን ይደመራል ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ፣
   - ወንጀሉ በተሰረቀው ሰው ወይም ድርጅት ስራ አደጋ ላይ የጣለ ከሆነ (2 እርከን ጭማሪ) እና የተሰረቀው ንብረት ፊንጂ ወይም ተቀጣጣይ ከሆነ (2 እርከን ጭማሪ) በድምሩ 4 እርከን ያስጨምራል ማለት ነው፡፡
   - ስለሆነም የወንጀል ደረጃው 1 ለሆነው የቅጣት እርከኑ 6 ይሆናል፡፡
   - የወንጀል ደረጃው 2 ለሆነው የቅጣት እርከኑ 8 ይሆናል፡፡
   - ወዘተ

<u>በ669 መሰረት ቅጣት አወሳሰን፣</u>

በዚህ ድንጋጌ መሰረት ዳኛው ቅጣት ለመወሰን የሚጠቀምባቸው መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡ 1) የገንዘቡ መጠን፣ 2) የተሰረቀው እቃ አይነት፣ 3) ድርጊቱን የፈጸመው አድራጊ ማንነት፣ 4) የወንጀል አፈጻጸሙ ነው፡፡

ስለሆነም በ669 መሰረት ጥፋተኛ ነው ተብሎ ከተወሰነ በኋላ ቅጣቱ ሲወሰን ከተራ ቁጥር 2 እስከ ተራ ቁጥር 4 ያሉት ማክበጃዎች ስለሆኑ በዚህ ደረጃ አንድ ማክበጃ፣ ሁለት ማክበጃ ወይም ሶስት ማክበጃ ተብለው ተለይተዋል፡፡

<u>ምሳሌ</u>

1. ወንጀል አድራጊው የሰረቀው ብር 2000 የሚያወጣ ነው፡፡
2. የተሰረቀው እቃ አይነት በ669 (1) ውስጥ ከተዘረዘሩት ዝርዝሮች ውስጥ የሚካተት አይደለም፡፡
3. የወንጀል አድራጊው ማንነት የወኪልነት ስልጣን የተሰጠው ሆኖ በእጁ የገባውን ንብረት ላይ ነው፡፡
4. በድርጊቱ አፈጻጸም አንጻር በ669(3) ውስጥ የሚወድቅ አይደለም፡፡

ስለሆነም ሁለት ነገሮች ተለይተዋል፡፡

1. የገንዘቡ መጠን ብር 2000 ይገመታል፡፡
2. አንድ ማክበጃ ተሟልቷል፡፡

ስለሆነም፣

- በ669 መሰረት እስከ ብር 2000 ሆኖ አንድ ማክበጃ የተሟላ ከሆነ የወንጀል ደረጃው 2 ነው፡፡
- በ669 የወንጀል ደረጃው 2 የሆነ የመነሻ ቅጣት እርከኑ 9 ነው፡፡
- የቅጣት እርከን 9 ቅጣት ከ1አመት ከ4 ወር- 1 አመት ከ8 ወር ነው፡፡ ስለሆነም ዳኛው በዚህ ማእቀፍ ውስጥ ቅጣቱን ይወስናል ማለት ነው፡፡

<u>4.3.4. የውንብድና ወንጀሎችን በተመለከተ ቅጣት አወሳሰን፣</u>

<u>በ670 መሰረት ቅጣት አወሳሰን</u>

የውንብድና ወንጀል ጥፋተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ቅጣቱን ለመወሰን ዳኛው ከግምት የሚያስገባው ሁለት መስፈርቶችን ነው፡፡ እነርሱም፣

1. በወንጀሉ ለማግኘት የተፈለገው የንብረት መጠን ግምት፣ (ይህ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ድረስ በገንዘብ ግምት ተለይቶ ተቀምጧል፡፡
2. የሀይል አጠቃቀሙ፡፡ ይህንን በተመለከተ ሀይል የተጠቀመው እንዴት ነው ለሚለው ሶስት መስፈርቶች ተዘጋጅተዋል፡፡ እነርሱም 1) መሳሪያ ሳይዝ ከሆነ ዝቅተኛ፣ 2) መሳሪያ ይዞ ከሆነ መካከለኛ፣ 3) የጦር መሳሪያ ይዞ ከሆነ ደግሞ ከፍተኛ ይባላል ማለት ነው፡፡

<u>ምሳሌ 1</u>

1. ወንጀል አድራጊ ብር 8000 የሚገመት ገንዘብ ወስዷል፡፡
2. የሀይል ተግባሩ የተፈጸመው መሳሪያ በመያዝ ነው፡፡ (መካከለኛ የሚባል የሀይል አጠቃቀም ነው)

እነዚህ ሁለት መስፈርቶች ተሟልተው የሚገኙበትን በሰንጠረዥ ስንመለከት የምናገኘው

- የወንጀል ደረጃ 3 ነው፡፡
- የወንጀል ደረጃ 3 ደግሞ የቅጣት እርከኑ 11 ነው፡፡
- በቅጣት እርከን 11 ደግሞ ቅጣቱ ከ1 አመት ከ8 ወር -2 አመት ከ2 ወር ነው፡፡ ስለሆነም ዳኛው በዚህ ውስጥ ቅጣቱን ይጥላል ማለት ነው፡፡

<u>ምሳሌ 2</u>

1. ወንጀል አድራጊው ብር 8000 የሚገመት ገንዘብ ወስዷል፡፡
2. ወንጀሉ ሲፈጸም የሀይል ተግባሩን ለመፈጸም የጦር መሳሪያ ይዞ ነው፡፡

እነዚህ ሁለት መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ በ670 መሰረት፣

- የወንጀል ደረጃው ደረጃ 4 ነው፡፡
- የወንጀል ደረጃ 4 የቅጣት እርከኑ 13 ነው፡፡
- የቅጣት እርከን 13 የቅጣት መነሻ ከ2 አመት ከ3 ወር- 2 አመት ከ9 ወራት ነው፡፡ ስለሆነም ዳኛው በዚህ ሬንጅ ውስጥ ቅጣቱን ይወስናል ማለት ነው፡፡

**<u>በ671 መሰረት የቅጣት አወሳሰን</u>**

በዚህ መሰረት ቅጣት ለመወሰን የተቀመጡ መስፈርቶች አሉ፡፡ እነርሱም፣

1. የገንዘብ መጠኑ፣
2. ወንጀሉ በቡድን መፈጸሙ ወይም የተጠቀመበት መሳሪያ ናቸው፡፡

**<u>ምሳሌ 1.</u>**

1. የገንዘብ መጠኑ እስከ ብር 2000 ከሆነ
2. ወንጀሉ በቡድን የተፈጸመ ከሆነ

በ671- የወንጀል ደረጃ 1 ላይ ይወድቃል፡፡ ይህም በቅጣት እርከን 21 ላይ ይወድቃል ማለት ነው፡፡

**<u>ምሳሌ ቁ.2</u>**

1. የገንዘብ መጠኑ እስከ ብር 2000 ከሆነ
2. የሀይል ተግባሩን ለመፈጸም ጉዳት የሚያደርስ መሳሪያ ተጠቅሞ የአካል ጉዳት ያደረሰ ከሆነ፣

በ671- የወንጀል ደረጃ 2 ውስጥ ይወድቃል፡፡ የቅጣት እርከኑም 22 ነው፡፡

## <u>4.4. ደረጃ ላልወጣላቸው ወንጀሎች የቅጣት አወሳሰን</u>

ደረጃ ላልወጣላቸው ወንጀሎች ጥፋተኛነቱ ከተረጋገጠ በኋላ ዳኛው የሚያደርገው የሚከተለውን ነው፡፡

1. በወንጀል ድንጋጌው ከተቀመጠው መስፈርት አንጻር ወንጀሉን ዝቅተኛ፣ መካከለኛ ወይም ከባድ ብሎ ይለያል፡፡ ለዚህም ምክንያቱን ያስቀምጣል፡፡
2. በወንጀል ህጉ የተቀመጠውን ቅጣት ከመነሻው እስከ መድረሻው ለአራት እኩል ይከፍላል፡፡ (እርከን 1፣ እርከን 2፣ እርከን 3 እና እርከን 4 ይባላሉ፡፡)

3. በመቀጠል ‹ዝቅተኛ› ለሆነው በእርከን አንድ ውስጥ ቅጣት ይወስናል፣ ‹መካከለኛው› ለሆነው በእርከን ሁለት ውስጥ ቅጣት ይወስናል፣ ‹ከባድ› ለተባለው በእርከን ሶስት ውስጥ ቅጣት ይወስናል፡፡
4. ከዚህ በመቀጠል፣ የወሰነው ቅጣት በአባሪ አንድ በተያያዘው ሰንጠረዥ የሚወድቅበትን ዝቅተኛ እርከን ይለይና የተቀጣበትን እርከን ያስቀምጣል፡፡ (ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች ከሌሉ ይህ አያስፈልግም፡፡)

<u>**ምሳሌ**</u>

1. ወንጀሉ የተፈጸመው አስገድዶ መድፈር ሲሆን፣ በ620 (1) መሰረት ጥፋተኛ ተብሏል፡፡
2. በ620 (1) መሰረት ቅጣቱ ከ5 አመት እስከ 15 አመት ነው፡፡
3. ዳኛው ከተፈጸመው የአስገድዶ መድፈር ወንጀል አንጻር፣ ለምሳሌ
   - በወንጀሉ ምክንያት የወንጀሉ ሰለባ የሆነችው ሴት ወንጀል የፈጸመባትን ሰው የምታውቀውና የምታምነው በመሆኗ እናም
   - ወንጀሉ ሊፈጸምባት ሲሞከር ባደረገችው መከላከል ሀይል በመጠቀም ቀላል የአካል ጉዳት የደረሰባት በመሆኑ፣

   ወንጀሉን የሚያከብደው ስለሆነ በማለት ምክንያቱን ካስቀመጠ በኋላ <u>‹መካከለኛ›</u> አፈጻጸም ተብሎ ተሰይሟል በማለት ምክንያቱን ያስቀምጣል እንበል፡፡
4. በመቀጠል ከአምስት አመት እስከ አስራ አምስት አመት ያለው ልዩነት 10 አመት ነው፡፡ ይህ ለአራት ሲካፈል እያንዳንዱ ሁለት አመት ከ6 ወር ይሆናል፡፡ ስለሆነም
   - እርከን አንድ-- ከ5 አመት እስከ 7 አመት ከ6 ወር
   - እርከን ሁለት-- ከ7 አመት ከ6 ወር እስከ 10 አመት
   - እርከን ሶስት-- ከ10 አመት እስከ 12 አመት ከ6 ወር
   - እርከን አራት ከ12 አመት ከ6 ወር እስከ 15 አመት ይሆናል፡፡
5. ዳኛው ‹መካከለኛ› የወንጀል አፈጻጸም በማለት የመደበው ስለሆነ የሚወድቀው በእርከን 2 ውስጥ ነው፡፡
6. እርከን ሁለት ከ7 አመት ከ6 ወር እስከ 10 አመት ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ውስጥ ቅጣቱን ይወስናል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም 8 አመት ነው በማለት ወስኗል እንበል፣
7. 8 አመት እስራት እርከን 25 እና 26 ውስጥ ይወድቃል፡፡
8. መመሪያው ዝቅተኛውን እርከን እንዲመረጥ ስለሚያዝ እርከን 25 ይመረጣል ማለት ነው፡፡ (ማክበጃ እና/ወይም ማቅለያ ምክንያቶች ካሉ ለማክበድ ወይም ለማቅለል)

## የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ በሚኖርበት ጊዜ የቅጣት አሰላል፣

ዳኛው መነሻ ቅጣቱን ከወሰነ በኋላ የቅጣት ማክበጃዎች ሲኖሩ ምን ማድረግ እንዳለበት እንዲሁም የቅጣት ማቅለያ ሲኖር ምን ማድረግ እንዳለበት በመመሪያው ተቀምጧል፡፡

### 4.5.1. ጠቅላላ ማክበጃና ማቅለያ በሚኖርበት ጊዜ የቅጣት አሰላል፣

1. ጠቅላላ ማክበጃዎችን በሚመለከት፣

በመመሪያው እንደተመለከተው፣

1. በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 84 በአምስት ንኡሳን አንቀጾች የተቀመጡት ምክንያቶች እያንዳንዳቸው እንደአንድ ማክበጃ ምክንያቶች ተወስደዋል፡፡ ማለትም በዝርዝሩ ውስጥ ከተመለከቱት ሁሉም ቢሟሉም፣ በከፊል ቢሟሉም አንዱ ብቻ ቢሟላም እንደአንድ ማክበጃ ምክንያት የሚወሰድ ነው፡፡
2. በዚህ ማክበጃ ምክንያት መሰረት በማድረግ ቅጣቱ የሚከብደው በአንድ የቅጣት እርከን ነው፡፡
3. ስለሆነም በሚኖረው የማክበጃ ቁጥር መሰረት ቅጣቱ ይከብዳል ማለት ነው፡፡

ምሳሌ ቁ 1

1. የተፈጸመው ወንጀል ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ ነው፡፡ (አንቀጽ 555)፡፡
2. የተፈጸመው ወንጀል ደረጃ 6 ሲሆን የቅጣት እርከን 23 ነው እንበል፡፡
3. በማስረጃ ተረጋግጠው የቀረቡ የቅጣት ማክበጃዎች፣
    - በስግብግብነት፣
    - በተለየ ክፋት ወይም ጨካኝነት
    - የጦር መሳሪያ በመጠቀም ከሆነ
4. ከዚህ በላይ በተመለከተው መሰረት የተዘረዘሩት ምክንያቶች ሶስት ቢሆኑም በማክበጃነት ያሉት ምክንያቶች 2 ናቸው፡፡ (ስግብግብነትና የተለየ ክፋት ወይም ጨካኝነት በአንድ ድንጋጌ ውስጥ የተመለከቱ በመሆናቸው)[16]
5. ስለሆነም ዳኛው በሁለት እርከን ወደላይ ቅጣቱን ከፍ ያደርጋል ማለት ነው፡፡ እርከን 23 የነበረው እርከን 25 ይሆናል ማለት ነው፡፡

[16] እነዚህ ምክንያቶች ወንጀሉን ለማቋቋምና መነሻ ቅጣቱን ለመወሰን አገልግለው ከሆነ አሁን በድጋሚ በማክበጃነት አይጠቀሱም፡፡

ጠቅላላ ማቅለያዎችን በሚመለከት፣

1. በቀላል እስራት ለሚያስቀጡ በአንድ ማቅለያ አንድ እርከን ይቀንሳል፡፡
2. የቅጣት መነሻቸው 1 አመት ጽኑ እስራት ለሆነ በእያንዳንዱ ማቅለያ ሁለት እርከን ይቀንሳል፡፡ ይሁንና ከስድስት ወር ጽኑ እስራት በታች አይወርድም፡፡
3. የቅጣት መነሻቸው ከአንድ አመት ጽኑ እስራት በላይ እስከ 7 አመት ጽኑ እስራት ለሆኑ ለእያንዳንዱ ማቅለያ በ2 እርከን ይቀንሳል፡፡ ይሁንና ከአንድ አመት ጽኑ እስራት በታች አይወርድም፡፡
4. የቅጣት መነሻቸው ሰባት አመትና ከሰባት አመት በላይ ለሆኑ ወንጀሎች በእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሶሰት እርከን ይቀነሳል፡፡ ይሁንና ከአንድ አመት ጽኑ እስራት በታች አይወርድም፡፡
5. የቅጣት መነሻቸው እድሜ ልክ ጽኑ እስራት ለሆኑ ወንጀሎች በእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሶስት እርከን ይቀነሳል፡፡ ይሁንና ቅጣቱ ሲቀል ከአስር አመት በታች አይወርድም፡፡
6. የቅጣት መነሻቸው የሞት ቅጣት ለሆኑ ወንጀለኞች በእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አራት እርከን ይቀነሳል፡፡ ይሁንና ቅጣቱ ሲቀል ከሃያ አመት በታች አይሆንም፡፡

ምሳሌ

1. ጥፋተኛው በቸልተኝነት ሰውን በመግደል ወንጀል በመፈጸም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 543 (1) መሰረት ጥፋተኛ ተብሎ ተወስኗል፡፡
2. ዳኛው የፈጸመው ወንጀል ‹ዝቅተኛ› በሚል የወሰነ ሲሆን፣ ዝቅተኛ ለሆነው ወንጀል መነሻ ቅጣቱን በእርከን አንድ ከ6 ወር እስከ 1 አመት ከ3 ወር ባለው ውስጥ 1 አመት በማለት ወስኗል፡፡
3. በመመሪያው መሰረት 1 አመት እስራት ቅጣት የሚወድቅበት እርከን 6 እና 7 ሲሆኑ ዝቅተኛው እርከን 6 (ከ8 ወር-1 አመት) እንደሚሆን ታውቋል፡፡
4. የቀረቡ የማቅለያ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡
    - ከዚህ በፊት የነበረው የዘወትር ጸባይ መልካም ነበር፡፡
    - ወንጀሉን ያደረገው ባልታሰበና ድንገተኛ አጋጣሚ ነው፡፡

- ወንጀሉን ከፈጸመ በኋላ በእውነት በመጸጸት ወንጀል ለደረሰበት አስፈላጊውን እርዳታ አድርጓል፡፡

5. ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ሶስት ምክንያቶች ቢጠቀሱም፣ ሁለቱ በንኡስ አንቀጽ 82(1)(ሀ) ውስጥ የሚካተቱ ስለሆነ እንደ አንድ ማቅለያ ምክንያት ነው የሚታዩት፡፡ ስለሆነም ሁለት ማቅለያ ምክንያቶች አሉት፡፡
6. ወንጀሉ የሚያስቀጣው በቀላል እስራት ስለሆነ ለእያንዳንዱ ማቅለያ የሚደረገው ቅናሽ አንድ እርከን ነው፡፡ ስለሆነም ለሁለት ማቅለያ በሁለት እርከን ሲቀንስ እርከን 4 (ከ4 ወር-7 ወር) በሚለው ውስጥ ይወድቃል፡፡
7. ዳኛው ቅጣቱን በዚህ ውስጥ 4 ወር ብሎ ሊወስን ይችላል፡፡
8. ይህንን ወደግዴታ ስራ ወይም መቀጮ ሊቀይረው ይችላል ማለት ነው፡፡

### 4.5.2. ልዩ ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ የቅጣት አሰላል፣

#### 1. ተደራራቢነትን በተመለከተ፣

1. ተደራራቢ ሆኖ በ184 በተመለከተው መሰረት የሚደመር በሆነ ጊዜ ዳኛው ለእያንዳንዱ ወንጀል ቅጣት መነሻ ካስቀመጠ በኋዋላ እነዚህን በመደመር የሚደርስበት ቅጣት የሚወድቅበት እርከን ላይ ቅጣቱ ይቀመጣል፡፡

**ምሳሌ፣**

- ጥፋተኛው በአንደኛው ወንጀል 2 አመት፣ በሁለተኛው ወንጀል 3 አመት መነሻ ቅጣት ይወሰናል፡፡
- እነዚህ ሲደመሩ 5 አመት ይሆናል፡፡
- 5 አመት በቅጣት እርከን 20 እና 21 ውስጥ ይወድቃል፡፡ ስለሆነም ዝቅተኛው ማለትም እርከን 20 የቅጣት መነሻው የሚያርፍበት እርከን ይሆናል ማለት ነው፡፡
- ከዚህ በመቀጠል በማስረጃ ተረጋግጠው የቀረቡ ጠቅላላ ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ ቅጣቱ ይሰላል፡፡

2. ተደራራቢ ጥፋቱ በ187 ንኡስ አንቀጽ አንድ ሁለተኛ ፓራግራፍ ወይም ንኡስ አንቀጽ 2(ለ) ከሆነ፣
   - ዳኛው ለከባዱ ወንጀል መነሻ ቅጣት ካስቀመጠ በሁዋላ ለከፍተኛው ወንጀል ከተቀመጠው ጣሪያ ሳይበልጥ በሁለት እርከን ያከብዳል፡፡

- ቀጥሎም ጠቅላላ ማክበጃ ምክንያቶችን መሰረት አድርጎ በእያንዳንዱ ምክንያት በአንድ እርከን ያሳድጋል።

**ምሳሌ፣**

- ሁለት ጣምራ ወንጀሎች በቸልተኝነት ተፈጽመዋል። (ይህ በአንቀጽ 187(2)(ለ) ውስጥ የሚወድቁ ናቸው።
- ደረጃ ለወጣላቸው የሚወድቁበት እርከን ስለሚቀመጥ ሁለት እርከን ጨምሮ ቅጣቱ ይወሰናል ማለት ነው።
- ደረጃ ላልወጣላቸው ለከባዱ ወንጀል የተወሰነው ቅጣት 2 አመት ነው እንበል
- 2 አመት እስራት ቅጣት የሚወድቀው እርከን 11 እና 12 ውስጥ ሲሆን፣ ዝቅተኛው እርከን 11 ይመረጣል።
- በመቀጠል ለሁለተኛው ወንጀል ሁለት እርከን ሲጨመር እርከን 13 ይሆናል ማለት ነው።
- ከዚህ በመቀጠል ጠቅላላ ማክበጃዎችና ጠቅላላ ማቅለያዎች ከአሉ ከዚህ በላይ በተመለከተው መሰረት ይሰላል ማለት ነው።

**2. ደጋጋሚነትን በተመለከተ፣**

- ደጋጋሚ ለሆነው በመመሪያው እንደተመለከተው ከአንድ እርከን ጀምሮ እጥፍ እስኪሆን ድረስ ቅጣቱን ያሳድጋል።
- በመቀጠልም ጠቅላላ ማክበጃ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ ቅጣቱን ያከብዳል።

**3. ልዩ ማቅለያ ምክንያት በሚኖር ጊዜ**

በወንጀል ሕጉ ቅጣትን በመሰለው እንዲያቀል በፈቀደ ጊዜ ፍርድ ቤቱ በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሰረት ሳይወሰን ቅጣቱን በማቅለል ይወስናል።

## 4.6. የቅጣት አሰላል ቅደም ተከተል (በማሳያ ምሳሌዎች ተደግፍ የቀረበ፣)

### 4.6.1. የወንጀል ደረጃ ለወጣላቸው የወንጀል አይነቶች

የወንጀል ቅጣቱ አሰላል ቅደም ተከተል፣

1. የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኂላ በዚህ መመሪያ በክፍል ሶስት በተመለከተው መሰረት የወንጀሉ ደረጃ ይወሰናል።

2. በመቀጠልም የወንጀሉ ደረጃ የሚወድቅበትን የቅጣት እርከን በአባሪ አንድ ከተያያዘው የቅጣት ሰንጠረዥ ላይ ይለያል፡፡
3. በመቀጠልም በእርከኑ በተቀመጠው የቅጣት መነሻና መድረሻ መካከል ባለው ፍቅድ ስልጣን (range) ውስጥ መነሻ ቅጣት ይወሰናል፡፡
4. በማስረጃ የተረጋገጡ ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ካሉ በዚህ መመሪያ መሰረት ቅጣቱን አክብዶ ቅጣቱ የሚደርስበትን እርከን በማስቀመጥ ቅጣቱ ይወሰናል፡፡
5. በመቀጠል በማስረጃ በተረጋገጡ ጠቅላላ ማክበጃ ምክንያቶች መሰረት እርከኑን በመጨመር ቅጣቱ ይወሰናል፡፡
6. በማስረጃ በተረጋገጡ ማቅለያ ምክንያቶች መሰረት የሚቀነሰውን እርከን በመለየት ወርዶ እርከኑ የሚያርፍበትን በመለየት ቅጣቱ ይወሰናል፡፡
7. የሚጣለው የእስራት ቅጣት እስከ ስድስት ወር ወይም ከስድስት ወር በታች በሚሆንበት ጊዜ በዚህ መመሪያ ተያይዞ በሚገኘው የቅጣት እርከን ሰንጠረዥ መሰረት በግዴታ ስራ እንዲለወጥ ሊወስን ይችላል፡፡
8. በቅጣት ማቅለያ ጊዜ የእስራት ቅጣትን ወደ መቀጮ መቀየር እንደሚቻል በህጉ በተደነገገው መሰረት ወደመቀጮ ሲቀየርም በዚህ መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡

<u>ምሳሌ 1</u>

- ጥፋተኛው የወ/ሕ አንቀጽ 665 በመጣስ ብር 3000 የሚያወጣ ንብረት በመስረቅ ተረጋግጦበታል፡፡
- ሁለት ማክበጃ ምክንያቶች መኖራቸው ተረጋግጧል፡፡
- ሶስት ማቅለያ ምክንያቶች መኖራቸው ተረጋግጧል፡፡

<u>ቅጣቱ የሚወሰንበት ቅደም ተከተል፣</u>

1. በወንጀሉ ከተገኘው ጥቅም አንጻር በ665 በወንጀል ደረጃ 3 ውስጥ ይወድቃል፡፡
2. የወንጀል ደረጃ 3 በቅጣት እርከን 6 ውስጥ የሚወድቅ ነው፡፡ የቅጣት እርከን 6 ቅጣት (ከ8 ወር-1 አመት ነው)

3. ዳኛው በዚህ ሬንጅ ውስጥ መነሻ ቅጣቱን ይወስናል፡፡ ለምሳሌ 10 ወር ሊሆን ይችላል፡፡ ሁለት ማክበጃ ምክንያቶች በመኖራቸው እርከኑን በሁለት ያሳድጋል፡፡ ስለሆነም

4. እርከን 6 የነበረው እርከን 8 ይሆናል (ከ1 አመት ከ2 ወር- 1 አመት ከ6 ወር)

ሶስት ማቅለያ ምክንያቶች ስላሉ እርከኑን በሶስት ይቀንሳል፡፡ ስለሆነም እርከን 5 ላይ ይወድቃል፡፡

5. እርከን 5 (ከ6 ወር--- 9 ወር)
6. በእርከኑ ውስጥ ቅጣቱን ይወስናል፡፡ ለምሳሌ 8 ወር በማለት ዳኛው ሊወስን ይችላል ማለት ነው፡፡

ስለሆነም 8 ወር ቀላል እስራት እንዲቀጣ ተወስኗል በሚል ውሳኔው ይቀመጣል ማለት ነው፡፡

**ምሳሌ 2፣**

ወንጀል አድራጊው በሁለት ወንጀሎች ጥፋተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

1. ጥፋተኛው በውንብድና ወንጀል 471 ጥፋተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
   - ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን በመያዝ እገልሀለሁ ብሎ አስፈራርቶ የአካል ጉዳት አድርሳል፡፤
   - የተገኘው ጥቅም ብር 1500 ነው፡፡
2. እንደገና 10000 በማታለል ወንጀል 690 ጥፋተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
3. አንድ ማክበጃ ምክንያት እና 3 ማቅለያ ምክንያቶች መኖራቸው ተረጋግጧል፡፡

**የቅጣት አወሳሰን ቅደም ተከተል**

1. በውንብድና ከተፈጸመው ወንጀል አንጻር በ671 የወንጀል ደረጃ 2 ውስጥ ይወድቃል፡፡
2. የወንጀል ደረጃ 2 የቅጣት እርከን 22 ነው፡፡
3. የቅጣት እርከን 22 ቅጣት መነሻና መድረሻ (ከ5 አመት ከ6 ወር- 6 አመት ከ7 ወር ነው)
4. ዳኛው በዚህ ውስጥ ቅጣቱን ይወስናል፡፡ ሲወሰን 6 አመት ይሆናል ብሎ ወስናል እንበል፡፡
5. ለማታለል ወንጀል ከገንዘቡ መጠን አንጻር በ690 በወንጀል ደረጃ 4 ውስጥ ይወድቃል፡፡
6. የወንጀል ደረጃ 4 ለእስራት ቅጣት እርከን 8 ውስጥ ነው፡፡ (ከ1 አመትከ2 ወር - 1 አመት ከ6 ወር)፡፡
7. ዳኛው እንበል 1 አመት ከ3 ወር ቅጣት አስቀመጠ፡፡
8. ለሁለቱ ወንጀሎች የተሰጠው ቅጣት ይደመራል፡፡ ለውንብድና ወንጀል የተቀመጠው መነሻ 6 አመትና የማታለሉ 1 አመት ከ3 ወር ሲደመር **7 አመት ከ3 ወር ይመጣል፡፡**

9. 7 አመት ከ3 ወር የሚወድቅበት እርከን 24 እና 25 ናቸው፡፡
10. ዝቅተኛው ስለሚመረጥ እርከን 24 ይሆናል፡፡

ጠቅላላ ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች ከዚህ ቀጥሎ እንደሚከተለው ይሰላሉ፡፡

1. አንድ ማክበጃ ምክንያት በመኖሩ በአንድ እርከን ሲያድግ የቅጣት እርከን 25 ውስጥ ይወድቃል፡፡
2. ሶስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ስለአሉ፣ ለከባዱ መነሻው 1 አመት ስለሆነ ለእያንዳንዱ ማቅለያ ምክንያት በሁለት እርከን ይቀነሳል፡፡ ስለሆነም ለሶስት ምክንያቶች 6 እርከን ሲቀነስ እርከን 19 ላይ ያርፋል፡፡
3. የእርከን 19 የቅጣት ሬንጅ (ከ4 አመት- 4 አመት ከአስር ወር) ነው፡፡ ዳኛው በዚህ ውስጥ ቅጣቱን ይወስናል፡፡ ለምሳሌ 4 አመት ከ6 ወር ሊሆን ይችላል፡፡
4. በማታለል ወንጀል በመቀጮ ለሚጣለው ቅጣት በእርከን 3 ውስጥ ማለትም ጣሪያው እስከ 3000 ብር ይላል፡፡ ስለሆነም ከብር 3000 ሳይበልጥ ቅጣቱ ይጣላል ማለት ነው፡፡

ስለሆነም በማጠቃለያው ወንጀል አድራጊው በ4 አመት ከ6 ወር ጽኑ እስራት እና 3000 ብር ቅጣት እንዲከፍል በሚል የቅጣት ውሳኔው ይቀመጣል ማለት ነው፡፡

### 4.6.2. ደረጃ ላልወጣላቸው የቅጣት አወሳሰን ቅደም ተከተል፣

1. የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በድንጋጌው ከተቀመጠው አንጻር የወንጀሉ ከባድነትን በተመለከተ ‹ዝቅተኛ› ወይም ‹መካከለኛ› ወይም ‹ከባድ› በማለት በቅድሚያ ዳኛው ይለያል፡፡
2. ዳኛው ከባድ፣ ዝቅተኛ ወይም መካከለኛ ለማለት ምክንያቱን ያስቀምጣል፡፡
3. በመቀጠል ጥፋተኛ በተባለበት የወንጀል ድንጋጌ መነሻና መድረሻ መካከል ያለውን ጊዜ ለአራት እኩል በመክፈል የቅጣት እርከኑን ከአንድ እስከ አራት ይለያል፡፡
4. ቅጣቱ የሚወሰንበትን እርከን በመለየት መነሻ ቅጣት ያስቀምጣል፡፡
5. የተቀመጠው መነሻ ቅጣት በአባሪ አንድ ከተያያዘው ሰንጠረዥ በየትኛው እርከን ላይ እንደሚወድቅ ይወስናል፡፡
9. በማስረጃ የተረጋገጡ ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ካሉ በዚህ መመሪያ መሰረት ቅጣቱን አክብዶ ቅጣቱ የሚደርስበትን እርከን በማስቀመጥ ቅጣቱ ይወሰናል፡፡

10. በመቀጠል በማስረጃ በተረጋገጡ ጠቅላላ ማክበጃ ምክንያቶች መሰረት እርከኑን በመጨመር ቅጣቱ ይወሰናል፡፡

11. በማስረጃ በተረጋገጡ ማቅለያ ምክንያቶች መሰረት የሚቀነሰውን እርከን በመለየት ወርዶ እርከኑ የሚያርፍበትን በመለየት ቅጣቱ ይወሰናል፡፡

12. የሚጣለው የእስራት ቅጣት እስከ ስድስት ወር ወይም ከስድስት ወር በታች በሚሆንበት ጊዜ በዚህ መመሪያ ተያይዞ በሚገኘው የቅጣት እርከን ሰንጠረዥ መሰረት በግዴታ ስራ እንዲለወጥ ሊወሰን ይችላል፡፡

13. በቅጣት ማቅለያ ጊዜ የእስራት ቅጣትን ወደ መቀጮ መቀየር እንደሚቻል በህጉ በተደነገገው መሰረት ወደመቀጮ ሲቀየርም በዚህ መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡

<u>ምሳሌ 1</u>

1. በወ/ሕ አንቀጸ 540 መሰረት ጥፋተኛ ተብሎ ተወስኗል፡፡
2. ሁለት ማክበጃ ምክንያቶችና ሁለት ማቅለያ ምክንያቶች መኖራቸው በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

<u>የቅጣት አሰላል ቅደም ተከተል</u>

1. ዳኛው ጥፋቱን እንደክብደቱ ዝቅተኛ ብሎ ሰይሟል፡፡
2. የወንጀል ድንጋጌው የቅጣት ሬንጅ ለአራት ይከፈላል፡፡
   - እርከን አንድ (ከ5---9 አመት)
   - እርከን ሁለት (ከ9–13 አመት)
   - እርከን ሶስት (ከ13- 16 አመት
   - እርከን አራት (ከ16-20 አመት ይሆናል፡፡
3. ዳኛው ጥፋቱን ዝቅተኛ ብሎ ስለሰየመ የመጀመሪያው እርከን ውስጥ 6 አመት ብሎ ወሰነ እንበል፡፡
4. 6 አመት በዋናው የቅጣት ሰንጠረዠ እርከን ውስጥ የትኛው ውስጥ እንደሚወድቅ እንለያን፡፤ (እርከን 21 እና 22 ናቸው)
5. ዝቅተኛው እርከን 21 ይወሰድና መነሻ ይሆናል፡፡
6. ሁለት ጠቅላላ ማክበጃ ምክንያቶች በመኖራቸው በሁለት እርከን ያድጋል፡፡ እርከን 23 ይሆናል፡፡
7. በወንጀሉ የቅጣት መነሻ አምስት አመት ነው፡፡ በመመሪያው አንቀጽ 16 ንኡስ አንቀጽ 6 የቅጣት መነሻቸው ከአንድ አመት በላይና ከ7 አመት ጽኑ እስራት በታች የሆኑ ለእያንዳንዱ

ማቅለያ ምክንያት ሁለት እርከን ይቀንሳል ይላል፡፡ ስለሆነም በእያንዳንዱ ማቅለያ ምክንያት ሁለት እርከን ይቀነሳል፡፡

8. በዚህ ጉዳይ ሁለት ማቅለያ ምክንያቶች ስላሉ በጠቅላላው 4 እርከን ይቀነሳል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም በማክበጃው ደርሶ ከነበረበት እርከን 23 አራት እርከን ሲቀነስ እርከን 19 ይሆናል፡፡
9. እርከን 19 ቅጣቱ ከ4 አመት- 4 አመት ከ10 ወር ነው፡፡ ስለሆነም ዳኛው 4 አመት ከ5 ወር ሊወስን ይችላል፡፡

በማጠቃለያው በአራት አመት ከአምስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስነናል በሚል የቅጣት ውሳኔው ይቀመጣል ማለት ነው፡፡

## 4.7. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

1. በሙከራ ደረጃ ለቀረ ወንጀል፣ ማነሳሳት እና አባሪነትን በተመለከተ ሁለት እርከን ዝቅ ብሎ የቅጣቱ መነሻ ይሆናል፡፡
2. ዳኛው በህጉ ከተቀመጡት ውጪ ያሉ ማቅለያ ወይም ማክበጃ ምክንያቶችን በሚጠቀም ጊዜ ለጠቅላላ ቅጣት ማክበጃና ማክበጃ በሚኖረው ስሌት መሰረት እርከኑን ይወስናል፡፡
3. ዳኛው፣ የወንጀል አፈጻጸሙም ሆነ ባህርይው በዚህ መመሪያ ደረጃ በወጣላቸው ሊወከል የማይችል ሆኖ ባገኘው ጊዜ ወይም በዚህ መመሪያ በተቀመጠው መሰረት ቅጣቱን መወሰን ፍትህ የሚዛባ ነው ብሎ ያመነ ከሆነ፣ ምክንያቱን በማስቀመጥ የተለየ ቅጣት ሊጥል ይችላል፡፡
4. ዳኛው በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሰረት መመሪያው ከሚያስቀምጠው በተለየ እርከን ላይ እንዲያርፍ በማድረግ በሚወስንበት ጊዜ ሁሉ፣ ይህንኑ ለሚመለከተው አካል ማስታወቅ ወይም መረጃውን ማስተላለፍ ይኖርበታል፡፡ ፍርድ ቤቶችም በዚህ መሰረት የሚያሰባስቡትን መረጃዎች ለጠቅላይ ፍርድ ቤት የማስተላለፍ ግዴታ እንዳለባቸው መመሪያው አስቀምጧል፡፡

## 4.8. የንብረት ግምት በተመለከተ

1. ወንጀሉ የተፈጸመው በውጭ ገንዘብ ላይ ከሆነ፣ የገንዘቡ ምንዛሪ መጠን ቅጣቱ ሊወሰን ባለበት ጊዜ ባለው ምንዛሪ መሰረት ይሆናል፡፡

2. በወንጀሉ የተወሰደው ንብረት በሚሆንበት ጊዜ የንብረቱን ግምት በተመለከተ ተከሳሹ ክርክር ካቀረበ እና የተከሳሹ ክርክር ተቀባይነት ቢያገኝ የቅጣት እርከኑን የሚቀየር ከሆነ እና በፍርድ ቤቱ እምነት በአቃቤ ህግ የቀረበው ግምት ምክንያታዊ ያልሆነና ፍትህን ያዛባል ብሎ ሲያምን የራሱን ግምት በማስቀመጥ የወንጀል ደረጃውንና የቅጣት እርከኑን ይወስናል፡፡
3. የንብረት ግምትን በተመለከተ ትክክለኛ ግምት ከማስቀመጥ አንጻር ክርክር ሊኖር እንደሚችል ይገመታል፡፡ ይሁንና ከዚህ አንጻር ሊነሱ የሚችሉ ስጋቶችን ለመቀነስ የሚያስችል አቀራረብ መመሪያው አለው፡፡
    - ደረጃን ለመወሰን የተቀመጠው የንብረት ግምት ከ- እስከ በሚል ስለሆነ ትክክለኛ ግምት ለማስቀመጥ መቸገር አያስፈልግም፡፡ ለምሳሌ ከብር 100 በላይ እስከ ብር 1000 ውስጥ ለሚወድቅ በተመሳሳይ ደረጃ ውስጥ ስለሚቀመጥ ብር 100፣ 200፣ 300፣ 500፣ 800 መሆኑ ልዩነት ስለማያመጣ በከፍተኛ ደረጃ ክርክርን ያቀለዋል ተብሎ ይገመታል፡፡
    - ከዚህ በተጨማሪ አቃቤ ህግ ያቀረበው ግምት ፍትህን ያዛባል ካልተባለ በስተቀር የአቃቤ ህጉን ግምት እንዲቀበለው፣ አለበለዚያ የራሱን ግምት አስቀምጦ እንዲወስን ስለሚያስቀምጥ ይህም በተወሰነ ደረጃ ስራውን ያቀለዋል ተብሎ ይገመታል፡፡

## ማጠቃለያ

በአገራችን ሲሰራበት ከነበረው የቅጣት አወሳሰን ልምድና ተሞክሮ አንጻር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያወጣው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ በተሟላ መልኩ ሲተገበር በአጠቃላይ በቅጣት አወሳሰን አዲስ ስርአት እንደሚዘረጋ ይገመታል፡፡ መመሪያው ቅጣትን የማጥበቅ ውጤት እንዳለውም መገመት ይቻላል፡፡ ይሁንና አዲስና ያልተለመደ በመሆኑ በተግባር ሲተረጎም የተለያዩ ያልተጠበቁ ውጤቶች እና ችግሮች ሊያጋጥሙትም ይችላሉ፡፡ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ የማዘጋጀት ስራ ተጀመረ እንጂ አላለቀም፡፡ ዋናው ስራ የሚሆነው ከዚህ በኋላ ያለው ነው፡፡

ጋይድላይን በመሰረቱ ምድብ (ካታጎሪ) መመስረት ነው፡፡ መሰረታዊና ተመሳሳይ ባህርይ ያላቸውን ለይቶ በመውሰድ በአንድ ምድብ (ካታጎሪ) ስር የሚያስቀምጥ ነው፡፡ መሰረታዊ ሊባሉ የማይችሉትን ደግሞ ይተዋቸዋል፡፡ ይህ በእርግጥ ትክክለኛ አመዳደብ ነው ወይስ አይደለም የሚለው በተግባር እየተፈተሸ ሲሄድ የሚረጋገጥ ነው፡፡

በአሜሪካ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ በተግባር እየተፈተሸና እየዳበረ መጥቷል፡፡ በአገራችንም የቅጣት አወሳሰን መመሪያው በተግባር እየተሞከረ፣

- ምድቦቹ ሊለወጡ ወይም ሊሻሻሉ ይችላሉ፡፡
- በመመሪያው ከተፈቀደው ፍቅድ ስልጣን (ሬንጅ) ለመውጣት ዳኞች የተጠቀሙባቸው ምክንያቶች አሳማኝ ሆነው ከተገኙ አጠቃላይ መመሪያ እንዲሆኑ በጋይድላይኑ ውስጥ ይካተታሉ፡፡
- ከተፈቀደው ፍቅድ ስልጣን (ሬንጅ) ለመውጣት ዳኞች የተጠቀሙት ምክንያቶች ተገቢ ካልሆኑ ወደፊትም ስራላይ እንዳይውሉ ጋይድላይኑ መመሪያ ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡

በዚህ መልኩ መመሪያው እየዳበረና እየተሻሻለ ከጊዜ ወደጊዜ የበለጠ ውጤታማ እየሆነ የሚሄድ ስለሆነ የሁሉም የፍትህ አካላት በመመሪያው መሰረት ለመስራት እንዲጥሩና እንዲተጉ ያስፈልጋል፡፡

## ዋቢ ሰነዶች (በኢንተርኔት የሚገኙ)


1. SENTENCING GUIDELINES AROUND THE WORLD.
2. UNITED STATES SENTENCING COMMISSION **GUIDELINES MANUAL**
3. Sentencing guideline council, magistrate's court sentencing guideline.
4. FIFTEEN YEARS OF GUIDELINES SENTENCING: An Assessment of How Well the Federal Criminal Justice System is Achieving the Goals of Sentencing Reform. U.S. Sentencing Commission http://www.ussc.gov/15_year/chap1.pdf
5. Sentencing Guidelines – Minnesota. Presentation to the Sentencing Guidelines Council. July 2004. See http://www.sentencing-guidelines. gov.uk/ docs/ meeting4_presentations.pdf

6. The federal sentencing guideline: ten years later . an introduction and commentary
7. Police, Prosecutors, Criminals, and Determinate Sentencing: The Truth about Truth-in-Sentencing Laws
8. **Reforming the U.S. Sentencing Guidelines after Blakely** http://ssrn.com/abstract
9. **SENTENCING GUIDELINES, JUDICIAL DISCRETION, AND CRIME** http://papers.ssrn.com/abstract=933377
10. Sentencing in Germany